# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 343 ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልልን ለመመስረት የቀረበው ምክረ ሃሳብ ጸደቀ

**ዘሳለም ግዛው**

አዲስ አበባ:- የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር የነበሩ 6 ዞኖችና 5 ልዩ ወረዳዎች በጋራ «የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል» በሚል ክልል ለመመስረት ላቀረቡት ጥያቄ ሕዝበ ውሳኔ እንዲደራጅና ውጤቱ ለምክር ቤቱ እንዲቀርብ ወሰነ፡፡

በአንድ ክልል የእንደራጅ አቤቱታን ያቀረቡት፤ የወላይታ፣ የጋሞ፣ የጎፋ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጌዴኦ፣ የኮንሶ ዞኖች፣ እንዲሁም፤ የደራሼ፣ የአማሮ፣ የቡርጂ፣ የአሌ እና የባስኬቶ ልዩ ወረዳ ናቸው፡፡

ምክር ቤቱ ትናንት ባካሄደው ስድስተኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ አመት፣ 1ኛ አስቸኳይ ጉባኤው፤ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልልን ለመመስረት የቀረበውን ምክረ ሃሳብ በአምስት ተቃውሞና በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል፡፡

ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችል የሕዝብን ይሁንታ ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሶ፤ በዚህ መሠረትም ከማንኛውም ተጽእኖ ነፃ በሆነ መልኩ ገለልተኛ በሆነው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አማካኝነት በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሕዝበ ውሳኔ እንዲደራጅ ወስኗል።

የሕዝብ ውሳኔው ውጤት ሪፖርትም ለምክር ቤቱ እንዲቀርብ፣ የሕዝብ ውሳኔው ሂደት ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና የሕዝብን ሰፊ ተሳትፎ ባረጋገጠ መልኩ እንዲጠናቀቅ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና የጸጥታ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ምክር ቤቱ አዟል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው በጋራ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የመመስረት ጥያቄው ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው እና አቀራረቡም ሕግን የተከተለ መሆኑን መገንዘቡን ምክረ ሃሳቡን ያቀረቡት የማንነት የአስተዳደር ወሰንና የሰላም ግንባታ ቋሚ ኮሚቴ ጸሐፊ አቶ ፍቅሬ አማን አመልክተዋል፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ገበቡ ገብሬ

# «ሕዝብን ከሕዝብ የሚለያዩ ችግሮችን እየነቀልን ችግኞችን እንተክላለን»

## - ወ/ሮ አዳነች አቤቤ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በየአካባቢው ሕዝብን ከሕዝብ የሚለያዩ ችግሮችን እየነቀልን ችግኞችን በመትከል የሕዝባችንን ማህበራዊ መስተጋብር በዘላቂ መደጋገፍና አብሮነት ማጎልበት ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ አስታወቁ፡፡

በአዲስ አበባ ደረጃ በአንድ ጀምበር አራት ሚሊዮን ችግኝ ተከላና የአረንጓዴ አሻራ ማጠቃለያ መርሀ ግብር በትናንትናው ዕለት ተከናውኗል፡፡

ከንቲባ አዳነች በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ተገኝተው ችግኝ በተከሉበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት በከተማ አስተዳደር ደረጃ ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል የተያዘ ቢሆንም እቅዱ የከተማውን ፈጥኖ የመልማት ፍላጎት አያሳካም በማለት ከዕጥፍ በላይ ለመትከል ታቅዶ በርካታ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ መቆየታቸውን አንስተዋል፡፡

በመሆኑም በተያዘው የክረምት ችግኝ ተከላ ዘመቻ አስራ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኝ የተተከለ ሲሆን፣ የአንድ ጀምበር አራት ሚሊዮን ችግኝ ተከላን ጨምሮ አስራ አምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን እንደሚደርስ አስታውቀዋል፡፡

በአዲስ አበባና በዙርያዋ በየዓመቱ እየተተከለ ያለው ችግኝ በከተማዋ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመቅረፍ በጎ አስተዋፅኦ ያላቸው በመሆኑ ከተማ አስተዳደሩ የሚተክላቸው ችግኞች የከተማዋን የአየር ንብረት የሚጠብቁ፣ ከተማዋን ውበትን በማላበስ ለምግብነትና ጥላ የሚሆኑ ችግኞች ላይ በማተኮር ላለፉት ዓመታት ሲሠራ ቆይቷል ብለዋል፡፡

«ሕዝብን ከሕዝብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ከፋይል

ቢልለኔ ስዩም

# ሕወሓት የሰላም ንግግሩን ለማደናቀፍ እየሠራ መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታወቀ

## - የዓለም ጤና ድርጅት ኃላፊው የሀሰት ትርክቶችን ከማስተጋባት እንዲታቀቡም ጠይቋል

**በፀጋዬ ጥላሁን**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት የሰላም ንግግሩን ለማደናቀፍ እየሠራ መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡ የዓለም ጤና ድርጅት ኃላፊው ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም የሃሰት ክሶችንና ትርክቶችን ከማስተጋባት እንዲታቀቡም አሳስቧል፡፡

ሕወሓት የሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

# ሚዲያን ለብሔራዊ ጥቅም ማዋልና ነፃነትን በኃላፊነት መጠቀም እንደሚገባ ተገለጸ

## - ዘጠነኛው የኢፕድ ስለኢትዮጵያ መድረክ በጎንደር ተካሂዷል

**ቸርነት ሁንዴሳ**

ጎንደር፡- ለአገራዊ አንድነት፣ ለኅብረተሰብ ለውጥ፣ ለገጽታ ግንባታና ዕድገት ጉልህ ሚና ያለውን ሚዲያ ያለምንም ልዩነት ሁሉም የአገሪቱ መገናኛ ብዙኃን ለብሔራዊ ጥቅም መከበር ሊያውሉት እንደሚገባና የተሰጣቸውን ነፃነትም በኃላፊነት መንፈስ ሊጠቀሙበት እንደሚገባ በዘጠነኛው የኢፕድ ስለኢትዮጵያ መድረክ ተሳታፊዎች ገለጹ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያዘጋጀው ዘጠነኛው ስለኢትዮጵያ የፎቶ ኤግዚቢሽንና የፓናል ውይይት መድረክ «የሚዲያ ሚና ስለኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ በትናትናው ዕለት በጎንደር ተካሂዷል።

ሚዲያን ለብሔራዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# ወጣቱ ትውልድ የተሠሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በባለቤትነት እንዲጠብቅ ጥሪ ቀረበ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ወጣቱ ትውልድ በርዕሰ ከተማዋ የተሠሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በባለቤትነት እንዲጠብቅ እና አገልግሎታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀም የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አባላት ጥሪ አቀረቡ፡፡

በትናንትናው ዕለት ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የመጡ የብልፅግና ወጣቶች ሊግ ኃላፊዎችና አባላት የለውጡ አመራር ሥልጣን ላይ ከወጣ ወዲህ በመዲናዋ የተገነቡና ግንባታ ላይ ያሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ጎብኝተዋል፡፡ የአብርሆት ቤተ መጻሕፍት፣ የወዳጅነት እና የአንድነት ፓርኮች፣ የቤተ መንግሥት መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት እና የሳይንስና ኪነ ጥበብ ማዕከል የጉብኝቱ አካል ነበሩ፡፡

ጉብኝቱ ላይ ያገኘናቸው የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ኃላፊዎችና አባላት ወጣቱ ትውልድ በርዕሰ ከተማዋ የተሠሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በባለቤትነት እንዲጠብቅ እና አገልግሎታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የጋምቤላ ክልል የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወጣት ሯች ጎች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፤ በአዲስ አበባ ከተማ አብርሆት ቤተ መጻሕፍት፣ የወዳጅነት ፓርክ፣ ሳይንስና ኪነ ጥበብ ሙዚየም፣ አንድነት ፓርክንና ግንባታው በመጠናቀቅ ላይ የሚገኘውን የቤተ መንግሥት መኪና ማቆሚያ ግንባታን መጎብኘቱን ገልጿል፡፡

ከጉብኝቱ ኢትዮጵያ በጥሩ ዕድገት ላይ እንደምትገኝና በርካታ በጎ ጅምሮች እንዳሉ መረዳቱን የገለፀው ሯች፤ ወጣቱ ዕድለኛ ሆኖ ለነዚህ ፕሮጀክቶች ባለቤት መሆን ችሏል፡፡ ይህ በአንዴ ተሠርቶ የሚያበቃ ነገር ስላልሆነ በወጣቱ ትውልድ አማካኝነት ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ብሏል፡፡


ሯች ጎች

አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች ወጣቱ ላይ ያተኮሩ መሆናቸውም ሌላው ትልቅ ዕድል ነው ያለው ወጣት ሯች፤ ወጣቶች ቦታዎችን መጎብኘትና ማየት ብቻ ሳይሆን የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነትም አለባቸው ሲል አሳስቧል፡፡

እንደ ወጣት ሯች ገለፃ፤ በዚህ በዋና ከተማዋ በአዲስ አበባ ካየናቸው ልምዶች በመነሳት በየአካባቢያችን እንዲህ ዓይነት ፕሮጀክቶች እንዲኖሩ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ በአካባቢያችን ያሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመቅረፍ ሕዝቡ ትኩረቱ ልማት ላይ ብቻ እንዲሆን ማስቻል አለብን፡፡

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ኃላፊ ፍፁም ግረፌ በበኩሏ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በማከናወን የወጣቱን የሥራ ባህል ማዳበር እና አርዓያ መሆን እንደሚቻል ከጉብኝቱ ተረድቻለሁ ብላለች፡፡

የጎበኘናቸው ፕሮጀክቶች ከዚህ በፊት ቦታዎቻቸው የቆሻሻ መጣያ ነበሩ ያለችው ወጣት ፍፁም፤ የተገነቡት ተቋማት በሙሉ ደግሞ ለወጣቱ ብሎም ለሕዝብ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ናቸው፡፡ ይህ ለወጣቶች


ፍፁም ግረፌ

ሌት ከቀን በመሥራት ውጤታማ መሆን እንደሚቻል የሚያስተምር ነው ብላለች፡፡

እንደ ወጣት ፍፁም ገለፃ፤ ጠቅላዩ ሚኒስትሩ በሁሉም መንገድ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሥራዎችን ሠርተው እያሳዩ ነው ያሉት፤ እነዚህ ፕሮጀክቶች የተገነቡት ለወጣቱ በመሆኑ ወጣቱ ትውልድ ፕሮጀክቶችን በአግባቡ እንዲጠቀምባቸው እና በባለቤትነት ሊጠብቃቸው እንደሚገባ መልዕክቷን አስተላልፋለች፡፡

ከወላይታ ዞን ጠበላ ወረዳ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ሚዲያ ሞኒተሪንግ ሥራ ሂደት ኃላፊ ወጣት ደጉ ወዳጅም በጉብኝቱ ላይ ተሳታፊ ነበር፡፡

እንደ ወጣቱ ገለፃ፤ አገር ባልተረጋጋችበትና ነውጥ ውስጥ ባለችበት ሁኔታ በጥቂት ዓመታት እንዲህ ዓይነት ትላልቅ ፕሮጀክቶች መገንባታቸው እንደሚያስደንቅ ገልፆ ወጣቶች መለወጥና ማሸነፍ እንደሚቻል በተግባር ተረጋግጦ ያየንበት እና ማሸነፍና መለወጥ እንደምንችል የተረዳንበት ነው ብሏል፡፡

ያየናቸው ፕሮጀክቶች ከግንባታ ጀምሮ የቦታ


ደጉ ወዳጅ

አመራረጣቸው ብሎም ውበት እንዲኖራቸው ለማስቻል የተሄደበት ርቀት እጅግ በጣም ጥሩ ነው ያለው ወጣት ደጉ፤ በውበት ደረጃ የተሠሩ ውጫዊ ገፅታዎች ሳይቀር አዲስ አበባን አዲስ አበባ የሚያስመስሉ እና ዕድገቷን የሚመጥኑ ናቸው ሲል ተናግሯል፡፡

እንደ ወጣት ደጉ ገለፃ፤ መሰል ፕሮጀክቶችንና የፅዳትና ውበቱን ጉዳይ በየአካባቢያችን ወርደን የምንተገብርበት አቅም እንዳለ ግንዛቤ የጨበጥንበት ነው፡፡ የጉብኝቱም ዓላማ ከየመጣንበት አካባቢ ያለውን ኅብረተሰብ በማሳተፍ መሰል ሥራዎችን እንዲከናወኑ ማድረግ ነው፡፡

ታላላቅ ፕሮጀክቶችን የእኔ ነው በሚል ስሜት በየአካባቢው በተጀመሩት ኮይሻና መሰል ፕሮጀክቶች ላይ በመረባረብ የአገርን ልማት ማፋጠን ይኖርብናልም ብሏል፡፡

ሁሉም ወጣት በሰከነ መንፈስ ኢትዮጵያዊነትን ቢያወድስ፣ ቢታትርና ቢሠራ የምንናፍቀውን ዕድገት፤ የምንመኘውን ብልፅግና ዕውን ማድረግ እንችላለን ያለው ወጣት ደጉ፤ ወጣቱ ትውልድ የተሠሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በአግባቡ ከመጠቀም ባለፈ በባለቤትነት እንዲጠብቅ መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

# «ሠራዊቱ የአገርን ሰላምና የሕዝብን ደኅንነት ለማረጋገጥ ከሚያደርገው አኩሪ ተጋድሎ ጎን ለጎን የሕዝብ ወገንተኝነቱን በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል»

*- ዶክተር አብርሃም በላይ*
*የመከላከያ ሚኒስትር*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአገር መከላከያ ሠራዊት የአገርን ሰላምና የሕዝብን ደኅንነት ለማረጋገጥ ከሚያደርገው አኩሪ ተጋድሎ ጎን ለጎን የሕዝብ ወገንተኝነቱን በተግባር እያረጋገጠ መሆኑን የመከላከያ ሚኒስትሩ ዶክተር አብርሃም በላይ ገለጹ።

ሚኒስትሩ ይህን ያሉት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው 64 ግለሰቦች የሚውል ዘመናዊ የመኖሪያ ቤት ሕንፃ ግንባታን ለማስጀመር በአዲስ አበባ ከተማ የመሠረት ድንጋይ በተጣለበት ወቅት ነው።

የሚገነቡት ቤቶችም በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቁና በዝቅተኛ ወጪ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አማካኝነት በተገጣጣሚ ቴክኖሎጂ ግንባታ እንደሆነ ተገልጿል።

የመከላከያ ሚኒስትሩ ዶክተር አብርሃም በላይ፤ የአገር መከላከያ ሠራዊት በመስዋዕትነቱ የአገርን ሰላም ለማረጋገጥ ሌት-ተቀን እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ሠራዊቱ የአገርን ሰላም ለማረጋገጥ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ጎን ለጎንም የዜጎችን ችግር በቅርበት የሚፈታበትን አማራጭ በመጠቀም ሕዝባዊነቱን በተግባር እያረጋገጠ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዜጎች የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ በሚያጋጥማቸው ቦታ ሁሉ የዜጎችን ሕይወት በማዳን የሕዝብ አለኝታ እንደሆነ ተናግረዋል።

በተጨማሪም ሠራዊቱ በተለያዩ ጊዜያት አቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወገኖች ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ አንስተዋል።

የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠለት የመኖሪያ ቤት ግንባታም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ለዜጎች እንዲተላለፍ የቅርብ ክትትል እንደሚደረግበት አረጋግጠዋል።

በብልጽግና ፓርቲ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ መለሰ አለሙ፤ ኢትዮጵያ ፈተናዎቿን በማሸነፍ ታላላቅ የልማት ሥራዎችን ከግብ በማድረስ ብልጽግናዋን እያረጋገጠች ነው ብለዋል።

የከተማ አስተዳደሩም የተለያዩ አማራጮችን



በመጠቀም የቤት አቅርቦቱን ማሳደግ ጨምሮ የነዋሪውን ችግር ለመቅረፍ ሰፊ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የመከላከያ ሚኒስቴርም የሚያስገነባው የመኖሪያ ቤት ሕንፃ አቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች ችግር በመፍታት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚሰጥ ተናግረዋል።

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ሥራ አስፈጻሚ ነፃነት ዳባ፤ ባለፉት 60 ቀናት በክፍለ ከተማው የዜጎችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል ብለዋል።

ከእነዚሁ የልማት ሥራዎች መካከልም ከ400 በላይ የሚሆኑ የአቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወገኖችን ቤት በማደስ ማስተላለፍ እንደተቻለም ገልጸዋል።

የመከላከያ ሚኒስቴርም አቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወገኖች የመኖሪያ ቤት ግንባታ መጀመሩን አመስግነው፤ ቤቱ ሲጠናቀቅም የዜጎችን ችግር በመፍታት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው መናገራቸውን የኢዜአ ዘገባ ያመለክታል።

# በክልሉ በሕወሓት ወረራ ምክንያት ያልተከበሩ በዓላትን በሚያካክስ መልኩ ለማክበር ዝግጅት መደረጉ ተገለጸ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ምክንያት ሳይከበሩ የታለፉትን ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ በዓላትን ሊያካክስ በሚችል መልኩ ለማክበር ዝግጅት መደረጉን የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡ በዛሬው ዕለት በክልሉ ሁሉም አካባቢዎች የቡሄ በዓል በድምቀት ይከበራል፡፡

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ኤርሚያስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ቡሄ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬና ሶለል በዓላትን ጨምሮ ከወርሀ ነሐሴ ጀምሮ እስከ መስከረም 21 ግሸን ደብረ ከርቤ በአሸባሪው ሕወሓት ምክንያት ዓምና ሳይከበሩ የቀሩትን ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላትን ሊያካክስ በሚችል መንገድ በደማቅ ሁኔታ ለማክበር ዝግጅት ተደርጓል፡፡

አቶ ኤርሚያስ፤ በክልሉ የቡሄ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬና ሶለል በዓላት በወርሀ ክረምት እንደሚከበሩ ጠቅሰው፤ እነዚህ በዓላት ካለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በኮሮናና በጦርነት ምክንያት ማክበር እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡ በተለይ ላሊበላ፣ ሰቆጣና ወልዲያ ባለፈው ዓመት በጠላት ተወረው የነበሩ በመሆኑ በቀጣናው በዓላትን ማክበር ብቻ ሳይሆን በሰላም ውሎ ለመግባትና እንደፈለጉ ለመቀሳቀስ አስቸጋሪ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

አቶ ኤርሚያስ እንዳሉት፤ በዓላቱ የሚከበሩት ከወልዲያ ዩኒቨርሲቲ፣ ከደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ፣ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ከአማራ ዩኒቨርሲቲ ፎረም ጋር በመተባበር ነው፡፡ በዓላቱም በጥናትና ምርምር፣ ሲምፖዚየም፣ የፓናል ውይይትና በመሳሰሉት ሁነቶች ይከበራሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር በአደባባይ የሚከበሩ ይሆናል፡፡

በዓሉ ሲከበር ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት የተፋዘዘውን የቱሪዝም እንቅስቃሴና በዚህ ምክንያት የተጎዳውን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት ታሳቢም ያደረገ ጭምር መሆኑን ጠቁመው፤ ሕዝቡ በዓላቱ ወደሚከበርባቸው አካባቢዎች እንዲያቀና ጥሪ መደረጉንም ተናግረዋል፡፡

በዓላቱ በሚከበርባቸው በደብረ ታቦር፣ በሰቆጣ፣ በላሊበላ፣ በወልዲያና ቆቦ ከተሞች ላይ ሰፊ ዝግጅት መደረጉን የገለጹት አቶ ኤርሚያስ፤ ሆቴልና ሬስቶራንቶችን ጨምሮ አጠቃላይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝግጁና


አቶ ኤርሚያስ መኮንን

ከተሞችም ጽዱ መሆናቸውን፣ የባህል አልባሳት ሽያጭ፣ የጌጣጌጥና ልዩ ልዩ ስጦታዎች ሽያጭ አቅርቦት በተለየ ሁኔታ መመቻቸቱን ተናግረዋል፡፡ ይህ የሥራ ዕድል ፈጠራን የሚያበረታታና በመንግሥትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ገቢን የሚያሳድግ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

እስካሁን ባለው መረጃ ከፍተኛ የአገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ያለው ግሸን ላይ በመሆኑ ከመስቀል በዓል ጀምሮ እስከ ግሸን ደብረ ከርቤ ድረስ በዓሉን ለማክበር ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓልም ነው ያሉት፡፡

ጠላት በአካባቢዎቹ በወረረበት ወቅት በከፍተኛ ሁኔታ ጉዳት ማድረሱን የገለጹት አቶ ኤርሚያስ፤ አሸባሪው ኃይል ባህሉ የእኔ ነው ብሎ በመነሳት እንዳይከበር እንቅፋት ከመሆኑም በላይ ሴቶች ላይም ወሲባዊ ጥቃት ፈጽሞ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ ባህልን ያህል ግዙፍ ሀብት በማደብዘዝ ተደብቆ ለማስመዝገብ እስከ መስረቅ ድረስ የደረሰ አስነዋሪ ተግባር በአሸባሪው የሕወሓት ቡድን መፈጸሙን አንስተዋል፡፡

አቶ ኤርሚያስ እንዳሉት፤ አሸባሪው ኃይል ሰርጎ በገባበት ወቅት በዓላቱ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዳይኖራቸው የባህል ማዕከላት የማውደም፣ አርቲስቶችን አሳድዶ የመግደል፣ ከፍተኛ የሆነ የሥነ ጥበብና ኪነ ጥበብ ቁሶችን የመዝረፍ፣ ትላልቅ ሙዚየሞችን ጨምሮ የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች የማውደም አስነዋሪ ተግባራትን ፈጽሟል፡፡

# የአስተዳደር ወሰኑ መካለል ለቀጣይ ልማት ጥሩ መሠረት የሚጥል መሆኑን ርዕሰ መስተዳድሩ አስታወቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአስተዳደር ወሰኑ መካለል ለሕዝብ የጋራ ተጠቃሚነት ቀጣይ ለሚሠራው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ጥሩ መሠረት የሚጥል መሆኑን የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ተናገሩ። በአዲስ አበባ ከተማና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የአስተዳደር ወሰን ማካለል ላይ በሁለቱ ወገኖች የተደረሰ ስምምነት ላይ ሕዝባዊ ውይይት ተካሂዷል።

በውይይቱም የአስተዳደር ወሰን መካለል ከዚህ ቀደም ሲነሳ የነበረውን አለመግባባት ለመፍታት፣ የሕዝቦችን አብሮ የመኖርና በጋራ መልማት የሚያጠናክር መሆኑ ተመልክቷል።

በአዲስ አበባ ከተማና ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን መካከል የአስተዳደር ወሰን ባለመኖሩ በተለይ መሠረተ-ልማት ዝርጋታና ወሳኝ የሆኑ የልማት ሥራዎችን ለመሥራት እንዲሁም የመሬት ወረራን ጨምሮ ሕገ-ወጥ ተግባራትን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮ መቆየቱ ተጠቁሟል፡፡ የአስተዳደር ወሰን መካለል የሕዝቦችን ማህበራዊ ትስስር የሚያጠናክር፣ ዘላቂ የሕዝቦችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መሆኑም ነው የተገለጸው፡፡

ይህ የወሰን ማካለል ሂደት ተግባራዊ ሲደረግም የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት፣ የኦሮሚያ ክልል ሕገ-መንግሥትና የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር እንደመነሻ የተወሰደ መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን፤ ይህም ለዘላቂ ሰላምና ልማት ከፍተኛ ሚና እንዳለውም ተጠቁሟል፡፡



**አቶ ሽመልስ አብዲሳ**

ሕዝባዊ የውይይት መድረኩን የመሩት የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ፤ የአስተዳደር ወሰን መካለሉ ከአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ነዋሪዎች ባሻገር ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ድል መሆኑን ተናግረዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ እስከ አሁን ይህ ወሰን ባለመኖሩ የሁለቱም ነዋሪ ሕዝቦች ላይ ጉዳት ሲደርስ መቆየቱን አስታውሰው፤ አሁን ትልቅ ስኬት ላይ ተደርሷል ብለዋል። ከሕዝብ ይልቅ የመሬትን ሀብት ብቻ በማሰብ ያለፉት ሥርዓቶች በሁለቱም ወገን ባሉ ነዋሪዎች ላይ ዘርፈ- ብዙ ጉዳቶች ሲያደርሱ መቆየታቸውንም ጠቁመዋል፡፡

«የተሠራው ሥራ ለአዲስ አበባ ከተማን ነዋሪ፣ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ነዋሪና እንደ አጠቃላይም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ድል ነው፤ ሁላችሁም እንኳን ደስ አላችሁ» ያሉት አቶ ሽመልስ፤ ይህ የአስተዳደር ወሰን በአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን መካከል የተቀመጠ ነው ብለዋል፡፡

እስከ አሁንም የአስተዳደር ወሰን አለመኖሩ የአዲስ አበባ ከተማና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ነዋሪዎችን እንዲሁም በዚህ አካባቢ ያሉ አርሶ አደሮችንም መጉዳቱን ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ባለፉት ሥርዓቶች የሚፈልገውን አገልግሎት አግኝቶ በነፃነት የኖረ ሕዝብ አይደለም ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ «የእኛ አርሶ አደርም እንደዛው፤ በሥርዓቱ የነበሩ ሰዎች ግን ለእነሱ በሚሆን መልኩና እነሱን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ሠርተው ነው የሄዱበት» ብለዋል፡፡ በተደጋጋሚ እንደተገለጸውም የእነሱ ማዕከል መሬት ነበር፡፡ ማዕከላቸው አዲስ አበባ ነዋሪም ሆነ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ነዋሪም አልነበረም ሲሉም ተናግረዋል፡፡

አገራዊ ለውጡን ተከትሎ ሥልጣን የያዘው መንግሥት ግን ለሕዝቡ የልማት፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥያቄ ተገቢ ምላሾችን በመስጠት ላይ መሆኑን ተናግረዋል። የአስተዳደር ወሰን ጉዳይም የሕዝቡ የረዥም ጊዜ ጥያቄ ሆኖ ቆይቶ ምላሽ ማግኘቱን አቶ ሽመልስ ገልጸዋል።

ከዚህ በኋላ በሁለቱም ነዋሪዎች ላይ በደል ማድረስም ሆነ የዘረፋ ተግባር መፈጸም የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ነው ያሉት።

ውሳኔው ለሕዝቡ ትልቅ ትርጉም ያለው መሆኑንም ጠቁመው፤ በቀጣይ ለሚሠሩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎች ታላቅ ሽግግር ይሆናል ብለዋል።

«የለውጡ መንግሥት፣ ብልጽግና ፓርቲ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራር፣ የክልላችን አመራርና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ያሉ አመራሮች በቅንጅት ጉዳዩን በጥልቀት በመመርመር፣ የአገር ሽማግሌዎችን በማሳተፍ በሳል በሆነ መንገድ ችግሩ ተፈቷል ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ከዚህ በኋላ በዚህም በዛም በኩል ሆኖ የፈለገውን በማድረግ፣ ዘረፋ በመፈጸምና ሕዝብን በመበደል የሚኖር አካል ካሁን በኋላ የለም ማለት ነው፡፡ ይህ ለአዲስ አበባም ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞንም ትልቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡ በቀጣይ ለምንሠራቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎች ትልቅ ሽግግር ነው ማለት ነው » ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ውሳኔውን መሬት ለማስያዝና ለነዋሪው የሚሰጠው የቀደመው አገልግሎት እንዳይቆራረጥ የጋራ ጽሕፈት ቤት እንደሚቋቋምም አቶ ሽመልስ ጠቁመዋል። ሕዝቡን በመሠረተ- ልማት ለማስተሳሰርም በቁርጠኝነት እንደሚሠራ አረጋግጠዋል፡፡

በአዲስ አበባና በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የአስተዳደር ወሰን የማካለሉ ሥራ የሕዝቦችን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ስምምነት ላይ መደረሱ ይታወቃል፡፡

# አገልግሎቱ ከ43 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ለመሰብሰብ ማቀዱን አስታወቀ

## - 160 አዳዲስ የገጠር ከተሞችና መንደሮችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ እየሠራ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በተያዘው በጀት አመት 43 ነጥብ1 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ። አገልግሎቱ 160 የሚሆኑ አዳዲስ የገጠር ከተሞችና መንደሮችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ እየሠራ መሆኑንም አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሽፈራው ተሊላ የተቋሙን የ2014 በጀት አመት የእቅድ አፈጻጸም፣ በ2015 በጀት እቅድ ዙሪያ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በ2014 በጀት አመት የተቋሙን ገቢ በማሳደግ ረገድ ከኃይል ሽያጭ ለመሰብሰብ ከታቀደው 23 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር 21 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የእቅዱን 88 በመቶ ማሳካት የቻለ ሲሆን፣ በቀጣዩ በጀት አመት 43 ነጥብ1 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ እየሠራ ይገኛል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ አገልግሎት ከማሳደግ አንጻር በበጀት አመቱ ትግራይን ጨምሮ ለ1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ደንበኞችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ለ367 ሺ 466 ደንበኞች ተጠቃሚ በማድረግ የእቅዱን 32 ነጥብ 84 አከናውኗል። 425 አዳዲስ የገጠር ከሞችንና መንደሮችን ኤሌክትሪክ እንዲያገኙ ለማድረግ ከታቀደው ውስጥ 214 ከተሞች ተጠቃሚ በማድረግ የእቅዱን 48 በመቶ ማሳካት ተችሏል። በበጀት አመቱ አጠቃላይ የደንበኞቹ ቁጥር 4 ሚሊዮን 304 ሺ 942 ደርሷል።

ተቋሙ አገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ ተግባራዊ ያደረገው የኢአርፒ (ERP) ሞጁል ወደሥራ አስገብቷል ያሉት አቶ ሽፈራው፤ ከሜትር ንባብ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ 2 ሺ ዲጂታል የንባብ መሣሪያዎች በሥራ ላይ ውለዋል ብለዋል።

በአገሪቱ የሚገኙ 50 ሺ የከፍተኛ የኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች ነባሩን ቆጣሪ በዘመናዊ ቆጣሪዎች (ስማርት) የመቀየር ሥራ የተጀመረ ሲሆን፣ እስካሁን ከአንድ ሺ 600 በላይ ቆጣሪዎች እንደተቀየሩ ነው ዋና ሥራ አስፈጻሚው ያስታወቁት።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር ያሉ የሥራ እንቅስቃሴዎችን አስመልክቶ እንዳብራሩት፤ የአዲስ አበባ ማከፋፈያ መልሶ ግንባታ አቅም የማሳደግ ፕሮጀክት አጠቃላይ አፈጻጸም 99 ነጥብ 25 በመቶ፣ የማስተላለፊያና የማከፋፈያ መልሶ ግንባታና አቅም ማሳደግ አጠቃላይ አፈጻጸሙ 52 ነጥብ 75 በመቶ ደርሷል ብለዋል።

አቶ ሽፈራው እንደተናገሩት፤ ከደንበኞችና ባድርሻ አካላት በቀረቡ ቅሬታዎች መሠረት 221 አመራሮችና ሠራተኞች ላይ ማጣራት አካሂዶ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ 120 ሠራተኞች ላይ እርምጃ ተወስዷል። ቀሪ 101 የሚሆኑ ሠራተኞች ጉዳያቸው በተቋሙ የዲሲፕሊን ኮሚቴ እየታየ መሆኑን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማትና በኃይል ስርቆት 759 የወንጀል ክሶችን ሲከታተል መቆየቱንና በወንጀሎቹ አገልግሎቱ አንድ መቶ 30 ሚሊዮን 984 ሺ 279 ብር ኪሳራ ደርሶበታል። ይህን ተከትሎ በ36 መዝገቦች ላይ ፍርድ ቤት ባስተላለፈው የመጨረሻ ውሳኔ በ64 ተከሳሾች ላይ ከ6 ወር እስከ 12 አመት ጽኑ እስራት እንደተወሰነባቸው ተናግረዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ በአሸባሪው ሕወሓት ቡድን በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ ከፍተኛ ስርቆትና ውድመት የደረሰ ሲሆን በኤሌክትሪክ ማሰራጫና ማከፋፈያ መሠረተ ልማት 437 ሚሊዮን 892 ሺ 947 ነጥብ 86 ብር ጉዳት ደርሷል። በተቋሙ ዕቃ ግምጃ ቤት፣ የዲስትሪክት ጽሕፈት ቤቶችና ማዕከላት ጥሬ ገንዘብን ጨምሮ 347 ሚሊዮን 784 ሺ 540 ነጥብ 42 ብር የሚገመት ንብረት ውድመትና ዘረፋ ተፈጽሞበታል። በአጠቃላይ አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ 49 ሚሊዮን 479 ሺ 394 ነጥብ 90 ብር ውድመትና ኪሳራ ደርሷል።

በተቋም ደረጃ ከደረሰው ውድመት አንጻር 87 ነጥብ 85 በመቶ በአማራ ክልል ሲሆን 12 ነጥብ 15 የሚሆነው በአፋር ክልል ነው። ተቋሙ ከኢነርጂ ሽያጭ ብቻ 463 ሚሊዮን 801 ሺ 906 ነጥብ 62 ብር ገቢ እንዲያጣ መደረጉን አስታውቀዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በ2015 በጀት አመት 43ነጥብ1 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ማቀዱን፤ 160 ለሚሆኑ አዳዲስ የገጠር ከተሞችና መንደሮች የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ፤ ዘመናዊ የንባብ ክፍያ ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑ ደንበኞች ብዛት ወደ 30 በመቶ ለማሳደግና በሰው ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን በ60 በመቶ ለመቀነስ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

# የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቹ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ

**ፋንታነሽ ክንዴ**



**የመግባቢያ ሠነድ የፊርማ ሥነ ሥርዓት**

ፎቶ፡ በሃዲስ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት በግጭት የወደሙ የትምህርትና ጤና ተቋማትን መልሶ መገንባት የሚያስችል ሀብት ከዳያስፖራው ለመሰብሰብ የሚረዳ የመግባቢያ ሰነድ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ጤና ሚኒስቴር ጋር ትናንት ተፈራርሟል።

በመርሃ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደገለጹት፤ በጦርነቱ ከአራት ሺ በላይ ትምህርት ተቋማት ላይ ጉዳት ደርሷል። ከዚህ ውስጥ አንድ ሺ 300 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ መውደማቸውን ገልጸዋል።

የወደሙትን የትምህርት ተቋማትን በተሻለ ደረጃ መልሶ ለመገንባት ሥራዎች ተጀምረዋል ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ በቀጣይ ዓመት 300 የሚደርሱ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ታቅዷል፤ ለዚህም በተለያየ መልኩ ሀብት ለማሰባስብ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ከኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ጋር የተደረገው ስምምነትም ዳያስፖራዎች የሚያደርጉትን ድጋፍ በተደራጀ መልኩ ለማሰባሰብ ያግዛል ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ከዳያስፖራውና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ሀብት በማሰባሰብ ሙሉ በሙሉ የወደሙትን አንድ ሺ 300 ትምህርት ቤቶች በአራት ዓመታት ገንብቶ ለማጠናቀቅ መታቀዱን ጠቁመዋል።

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የዚህ ሥራ ባለቤቶች መሆናቸውን እንደሚያምኑ ጠቅሰው፤ ባለቤትነታቸውም መሰል ችግር ሲፈጠር ገንዘብ ከመሰብሰብ ባለፈ ቀጣይነት ባለው መንገድ የአገሪቱን ልማት በማገዝ ከልመና ለማላቀቅ የሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ አለባቸው ብለዋል።

ሚኒስቴሩ ከዳያስፖራዎች ከሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ባለፈ እውቀታቸውን እንዲያካፍሉና በቴክኖሎጂ እገዛ እንዲያደርጉ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ለመልሶ ግንባታ የሚሰባሰበው ሀብትም በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚውል መሆኑን በመረዳት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለያየ መልኩ የተለመደ ትብብራቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተከሰተው ግጭት የጤና ተቋማት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በዚህም ምክንያት በእነዚህ ተቋማት አገልግሎት ሲያገኙ የነበሩ በርካታ ዜጎች ለችግር ተዳርገዋል ብለዋል።

እነዚህን ተቋማት ወደ ሥራ ለማስገባት በተደረገው ርብርብ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በግብአት፣ በመሣሪያና በገንዘብ 600 ሚሊዮን ሀብት ማሰባሰብ መቻሉን አስታውሰው፤ ጉዳት የደረሰባቸውን ጤና ተቋማት መልሶ ለመገንባት በተሠራው ሥራ ብዙ ጤና ተቋማትን ወደ አገልግሎት መመለስ ተችሏል ብለዋል።

እስካሁን ለተደረገው ድጋፍ ምስጋና ያቀረቡት ዶክተር ሊያ፤ አሁንም ወደ አገልግሎት ያልተመለሱ ጤና ተቋማትን ወደ አገልግሎት ለመመለስ ብዙ ሀብት ስለሚጠይቅ በውስጥና በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና አጋር አካላት ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሐመድ እንድሪስ፤ ዳያስፖራው ለአገሩ የሚያደርጋቸውን ተሳትፎ ማስተባበር የአገልግሎቱ ቀዳሚ ተግባር እንደሆነ ጠቁመዋል።

አገልግሎቱ ከተቋቋመ በኋላ ባሉት ጊዜያት ከ3 ነጥብ 46 ቢሊዮን ብር በላይ ከዳያስፖራዎች መሰብሰቡን ጠቁመው፤ በዘንድሮው ዓመት ብቻ ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን ተናግረዋል።

ዳያስፖራው በተለያየ መልኩ ለአገሩ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በትናንትናው ዕለት የተፈረመው ስምምነትም ዳያስፖራው በተበታተነ መልኩ ለተለያዩ አገራዊ ፕሮጀክቶችና ለመልሶ ግንባታ ሲያደርግ የቆየውን ድጋፍ በተደራጀ አሠራር አጠናክሮ እንዲቀጥል ያግዛል ብለዋል።



ዶክተር ይልቃል ከፋለ

# ርዕሰ መስተዳድሩ ለአሸንድዬ፣ ሻደይ እና ሶለል በዓላት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላለፉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ለአሸንድዬ፣ ሻደይና ሶለል በዓላት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላለፉ።

ርዕሰ መስተዳድሩ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት፣ ባህል የአንድ አካባቢ ሕዝቦች የአብሮነታቸው ማሳያና የማንነታቸው መገለጫ ከመሆኑ ባሻገር የለውጥና እድገት እንዲሁም የኪነጥበብና ሥልጣኔ ምልክት መሆኑን አውስተዋል፡፡

በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች አሸንድዬ፣ ሻደይና ሶለል በዓላት በልዩ ልዩ ባሕላዊ ክዋኔዎች እንደሚከበሩ የጠቀሱት ዶክተር ይልቃል፤ በዓሉ ወጣቶችና ልጃገረዶች አደባባይ ወጥተው፣ በአንድነት ተሰባስበው ባሕልና እሴቶቻቸውን በመግለጽ የሚያሳልፉበትና በመካከላቸው ጠንካራ የባሕል ትስስር የሚፈጥሩበት ነው ብለዋል።

በዓላቱ በሕዝቦች መካከል ማህበራዊ ትስስር በመፍጠር አንድነትን እንደሚያጠናክሩ የገለጹት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ በአንድነት ውስጥ መተዋወቅና መከባበርን፤ በመከባበር ውስጥ ደግሞ የጋራ ሰላምና ልማትን ይገነባሉ ነው ያሉት።

በዓላቱን ወቅት ጠብቀን ከማክበር ባለፈ በቅርስነት ጠብቀን፣ ለክልላችን ቱሪዝም ልማት እድገት የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ በአግባቡና በተገቢው መንገድ በማስተዋወቅ ልንጠቀምባቸው የሚገቡ እሴቶቻችን ናቸው ብለዋል።

ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል የአሸንድዬ፣ ሻደይ እና ሶለል በዓላት ሲከበሩ መረዳዳትና መደጋገፍ በተግባር የሚታይበት እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የደቡብ ኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ክልሉን ለመመስረት የወሰኑት ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች በየምክር ቤቶቻቸው በተናጠል ባካሄዱት ስብሰባ ምክክር ያደረጉበትና የተስማሙበት መሆኑን ከቀረበው ማስረጃ መረጋገጡንም አቶ ፍቅሬ ጠቅሰዋል፡፡

በአንድ ክልል መደራጀት አገራዊ ለውጡን ተከትሎ የተጀመረውን ዴሞክራሲና ልማት በጋራ ለማስቀጠል፣ ሕብረ ብሔራዊ አንድነትን በማጠናከር ዘላቂ ሰላም ለማስፈንና ጤናማ የፌዴራል ሥርዓት ከመገንባት አኳያ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው በምክረ ሃሳቡ ተብራርቷል፡፡

የምክር ቤቱ አፈጉባዔ አቶ አገኘሁ ተሻገር ከለውጡ በፊት በርካታ የሕዝብ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ባለማግኘታቸው ለግጭት መንስዔ ሲሆኑ መቆየታቸውን አስታውሰው፤ በአገር ሀብት እና በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ውድመትና ጥፋት ሲያደርሱ እንደነበርም ተናግረዋል፡፡

ሰላምን ለማስፈን፣ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመገንባትና በፍትሐዊነት ላይ የተመሠረተ ልማት ለማፋጠን የሕዝብ ጥያቄዎች በአፋጣኝ ሊመለሱ እንደሚገባም ተናግረዋል።

አገራዊ ለውጡን ተከትሎ ምክር ቤቱ ተቋማዊ ለውጥ በማድረግ ከሕዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች አፋጣኝ ሕገ መንግሥታዊ ምላሽ ለመስጠት ሰፊ ሥራ እየሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አገኘሁ፤ የሲዳማ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል እንሁን ጥያቄዎች የተመለሱበትን አግባብ ማስታወሱ አንዱ ማሳያ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

ምክር ቤቱ ትናንት አስቸኳይ ጉባኤ የጠራበት ዋና ምክንያትም ለሕዝቦች ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ካለው ቁርጠኝነት በመነሳት እንደሆነና በቀጣይም ከሕዝብ የሚነሱ ጥያቄዎች ቅድመ ሁኔታቸውን አሟልተው ሲመጡ አቤቱታቸውን በጥንቃቄ በመመርመር ምክር ቤቱ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የማንነት የአስተዳደር ወሰንና የሰላም ግንባታ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ጥላሁን ከበደ በበኩላቸው፤ ሂደቱ በጋራ ስምምነት ተደርጎበት የጋራ እቅድ ወጥቶ ወደ ተግባር የተገባበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በክልል እንደራጅ ጥያቄ ለመመለስ ስድስት መርሆዎችን በማዘጋጀት ኮሚቴ በማዋቀር መተግበሩንም አንስተዋል፡፡

ሂደቱ ሕዝቡን በሚገባ ያሳተፈና በተግባቦት የሚወሰን መሆን እንዳለበት፣ ከኢ-ፍትሃዊነትና ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት አኳያ የታየውን ችግር የሚፈታና በጥርጣሬ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት የሕግና የፖሊሲ ዝግጅት እንዲኖር በማድረግ የተፈጸመ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ከክልል በመለስ ያሉ የመዋቅር ጥያቄዎችን (የወረዳ፣ የከተማ፣ የዞንና የቀበሌ) አደራጅቶ መፍታት የሚችልበትን ሁኔታ የሚመለከት፣ የሚደራጀው ክልል ሁሉን የሚያማክልና የአገልግሎት ተደራሽነት እንዲኖር ከአንድ በላይ የክልል ማዕከላት እንዲኖሩ በሚያስችል መልኩ መከናወኑንም አንስተዋል፡፡

የሕዝብ ለሕዝብ ቀጣይ አብሮነትን በሚያጎላ፣ የመተጋገዝ፣ የመደጋገፍና የወንድማማችነት መንፈስን በሚያጠናክር መልኩ መፈጸሙን እንዲሁም ቅሬታዎች በሕዝቡ ባህል፣ ወግ፣ ሥርዓትና በሕግም የሚፈቱበትን አሠራር መከተሉንም ነው ያብራሩት፡፡

የሀድያ፣ ሀላባ፣ ከምባታና ጠምባሮ፣ ስልጤ፣ ጉራጌ ዞኖችና የም ልዩ ወረዳ በነባሩ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አንድ ላይ የሚቀጥሉ መሆኑም ታውቋል፡፡

# ሕወሓት የሰላም ንግግሩን ለማደናቀፍ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታርያት ኃላፊ ቢልለኔ ስዩም ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደገለጹት፤ መንግሥት ሰላምን ለማሳለጥ እና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ ነው። ለዚህም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሰላም ንግግር ለማካሄድ ዝግጁ ነው። ይህ ጥረት መንግሥት ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያረጋግጥ ነው።

የሰላም ንግግሩ በሁለቱም ወገን ቅድመ ሁኔታ አያስፈልገውም ያሉት ኃላፊዋ፤ ሆኖም ሕወሓት የራሱን ፍላጎት በኃይል ለማስፈፀም እየጣረ ነው ብለዋል። ይህም መንግሥት ለግጭቱ እልባት ለመስጠት ሰነድ ይፋ ባደረገበት ወቅት የሚያቀርበው የሀሰት ክስ የሰላም ንግግሩን ለማደናቀፍ ወይም ለንግግሩ ዝግጁ አለመሆኑን ያመላክታል ሲሉ ተናግረዋል።

ኃላፊዋ እንዳሉት፤ በሕወሓት በኩል የሰላም ጥረቶች ቦታ የላቸውም። መንግሥት በትግራይ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመር ፍላጎት ቢኖረውም ከሕወሓት በኩል የወረቀት ብቻ ሳይሆን የተግባር ማረጋገጫና መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች አሉ።

መንግሥት ቃል በገባው መሠረት የሰብአዊ እርዳታና ሌሎች ቁሳቁሶች ወደ ትግራይ ገብተው ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ እያደረገ ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ ነገር ግን ሕወሓትና ደጋፊዎቻቸው አሁንም ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማደናገር የሀሰት ክሶችንና ትርክቶችን በማስተጋባት ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ለመምራት ጥረት እያደረጉ ናቸው ብለዋል።

በሌላ በኩል የዓለም ጤና ድርጅት ኃላፊ ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም ስልጣናቸውን ተጠቅመው የአሸባሪው ሕወሓትን የሀሰት ትርክቶችና ክሶችን ደግፈው ከሚሰጡት አስተያየትና ንግግር እንዲታቀቡ ኃላፊዋ አሳስበዋል።

ኃላፊዋ እንደገለጹት፤ የዓለም ጤና ድርጅት ኃላፊ ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም ከድርጅቱ የሥነ-ምግባር መርህ ውጪ ስልጣናቸውን ተጠቅመው ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አዘኔታን ለማግኘት የሕወሓት የሀሰት ትርክቶችንና ክሶችን በማስተጋባት ላይ ናቸው። ግለሰቡ አሸባሪውን ወግነው የሚሰጡት አስተያየትና ንግግርም የድርጅቱን መርህ የጣሰ ነው ብለዋል።

ሆኖም ሥነ-ምግባር የጎደለው ንግግራቸውና አስተያየታቸው አዲስ አለመሆኑን የጠቆሙት ቢልለኔ ስዩም፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጽሕፈት ቤት ግለሰቡ እስካሁን ለፈጸሙት ሥነ-ምግባር የጎደለው ድርጊት ግምገማና ማጣራት እንደሚያደርግባቸው አንጠራጠርም ብለዋል።

የድርጅቱ መርህም ሠራተኞቹ በገለልተኝነትና ያለአድልኦ እንዲሠሩ ያስገድዳል ያሉት ቢልለኔ ስዩም፤ አንድ ዓለም አቀፍ ተቋምን የሚመራ ሰው የዘራፊውን ሕወሓት የውሸት ትርክት ደግፎ መቆምና ማስተጋባት ወንጀል በመሆኑ ግለሰቡ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ጠይቀዋል።

ግለሰቡ በድርጊታቸው ከቀጠሉ መንግሥት ጉዳዩን ወደ ሚመለከተው አካል ለመውሰድ ዝግጁ ነው ሲሉም አስረድተዋል።

# ሚዲያን ለብሔራዊ ጥቅም ማዋልና...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ፣ የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ እጸገነት መንግሥቱ እና የጎንደር ከተማ ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባ አቶ ዘውዱ ማለደ ከአጼ ኃይለሥላሴ እስከ ለውጡ ዘመን የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሂደት፣ ልማትና የአገር ሉአላዊነትን የማስከበር ዘመቻን የሚያመላክተውን የፎቶ ኤግዚቢሽን በጋራ ከፍተዋል።

«የሚዲያ ሚና ስለኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ በተካሄደውና የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትሩ ዶክተር ለገሰ ቱሉ በመሩት የፓናል ውይይት መድረክ «ሚዲያና ብሔራዊ ጥቅም» በሚል የመጀመሪያ የመወያያ ጽሑፍ ያቀረቡት ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ አራተኛው መንግሥት በመባል የሚጠራው ሚዲያ የአገር ብሔራዊ ጥቅም ከሚከበርባቸው መሣሪያዎች አንዱና ዋነኛው መሆኑን ገልጸው፤ ይህንንም በመረዳት አገራት ትኩረት ሰጥተው እንደሚሠሩበት ያደጉ አገራትን በምሳሌነት በማንሳት አስረድተዋል።

«በዚህ ዘመን ሥራችን ይናገራል ብሎ መቀመጥ አያዋጣም ይሄንኑ በሚዲያ በሚገባ ማሳወቅ ይገባል» ያሉት ፕሮፌሰር ብሩክ በተለይም አገራችን በቅርቡ ፈተናዎች ባጋጠማትና አላስፈላጊ የውጭ ጫናዎች በተበራከቱበት ወቅት ሁሉም የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃንና ዳያስፖራው ለብሔራዊ ጥቅም በጋራ የቆሙበት ሁኔታ የሚመሰገንና በሌሎችም የአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅሞች ዙሪያ ሊደገም የሚገባው ነው ብለዋል።

«የሚዲያ ነፃነትና ኃላፊነት» በሚል ርዕስ ሁለተኛውን የመወያያ ጽሑፍ ያቀረቡት ዶክተር አጋረደች ጀማነህ ሚዲያ የሚጠበቅበትን ድርሻ እንዲወጣ ነፃነት ወሳኝ መሆኑን በመግለጽ ሚዲያ ነፃነቱን ካጣና ከታፈነ የኅብረተሰብ እመርታ ይገታል ብለዋል። ነፃነት ለሚዲያ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም ነፃነቱን ግን ከኃላፊነት ጋር ሊወጣ እንደሚገባና ይህ የማይሆን ከሆነ ግን አገራዊ አንድነትንና ጠቃሚ እሴቶችን ከመሸርሸር አንስቶ አገር እስከማፍረስ የሚደርስ ጉዳት እንዳለው አስታውቀዋል። የሚዲያ ነፃነትን በአግባብ ለመጠቀምም የሕግ ማዕቀፎችን መዘርጋት፣ የብሮድካስትና የበጎ ፈቃደኝነት ቁጥጥር አስፈላጊ መሆናቸውንም አስታውቀዋል።

«የማህበራዊ ሚዲያ ስኬት ተግዳሮትና ዕድሎች» በሚል ርዕስ ሦስተኛውን የመወያያ ጽሑፍ ያቀረቡት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ መሃመድ እድሪስ የቴክኖሎጂ ዕድገት በሚዲያው ዘርፍ ካስገኛቸው ለውጦች አንዱ ሳይበር ስፔስና ማህበራዊ ሚዲያ መሆኑን ገልጸዋል። ማህበራዊ ሚዲያ መረጃን በስፋትና በፍጥነት ተደራሽ በማድረግ፣ የገቢ ዕድል በመፍጠርና ብሔራዊ ጥቅምን ለማስከበር በጋራ የሚቆምበትን ዕድል መፍጠሩ አዎንታዊ ጎኖቹ ሲሆኑ ለሀሰት መረጃ የተጋለጠ መሆኑ፣ ምርታማነትን መጉዳቱ፣ ከምክንያታዊነት ይልቅ ስሜታዊነት እንዲጎላ ማድረጉና የሚና መደበላለቅ መፍጠሩ አሉታዊ ጎኖቹ ናቸው ብለዋል። የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስም የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ዕውቀትን ማስፋፋትና እንደዘርፍ በፖሊሲ መምራት አስፈላጊ ነው የሚል ምክረ ሃሳብ አቅርበዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትሩ ዶክተር ለገሰ ቱሉ በማጠቃለያው የሚዲያ ነፃነት ሊኖር የሚችለው አገር ስትኖርና ደህና ስትሆን ነው ካሉ በኋላ ለብሔራዊ ጥቅምና ለኅብረብሔራዊ አንድነት ሚዲያ ያለምንም ልዩነት በጋራ መሥራትና ሕዝቦችን ከሚያጋጩና ከሚከፋፍሉ ጉዳዮች መራቅ እንዳለበት አሳስበዋል። የሚዲያ ነፃነት ከኃላፊነት ጋር አብሮ የሚሄድና አተገባበሩም በአገራት ተጨባጭና ወቅታዊ ሁኔታ እንደሚወሰንም አስረድተዋል።

# «ሕዝብን ከሕዝብ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የክረምት ዘመቻው ቢጠቃለልም ከተማዋን አረንጓዴ የማልበስ ተግባር ግን የሚቀጥል መሆኑን ከንቲባዋ አንስተው፣ አዲስ አበባን አረንጓዴ ማልበስ ሥራ የዘወትር ሥራ በመሆኑ ለውጤታማነቱ ማኅበረሰቡ ዘመቻ ሳያስፈልገው በየአካባቢው ሊተገበር የሚገባ ተግባር መሆን እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

በጋራ የምናሳርፈው አሻራ ለነገ ልምላሜ የሞላባት፣ ንፁህ አየር የሚተነፈስባት፣ የተፈጥሮ ምጥጥኗ የተጠበቀላት እንዲሁም ሕንፃና መሠረተ ልማቶች ብቻ ሳይሆኑ መንፈስን የሚያድሱ እፅዋትን በመትከል ውብ ከተማ ለመፍጠር የሚያስችል የጋራ የቃል ኪዳን አሻራ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ስንተባበር ታላቅ ሥራን የምናከናውን፣ ስንቀራረብ ደግሞ የምንበረታ፣ ስንደማመጥና ስንከባበር በጋራ እናሸንፋለን ያሉት ከንቲባዋ፣ በአረንጓዴ አሻራ ያሳየነው ኅብረት በሁሉም ሥራዎቻችን አጠናክረን በመቀጠል ከተማችን አዲስ አበባን እንደ ስሟ አዲስና ውብ ለማድረግ ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን መትጋት አለብን ብለዋል፡፡

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወ/ሮ ነፃነት ዳባ በበኩላቸው በክፍለ ከተማው የተተከሉ ችግኞችን መላውን ማኅበረሰብ በማስተባበር ችግኞችን ተክሎ መሄድ ብቻ ሳይሆን እንደ ከዚህ በፊቱ ሁሉ የፅድቀት መጠናቸው ከፍ እንዲል ክትትል እንደሚደረግ አስታውቀዋል፡፡

በችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ ላይ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አግኝቶ ካነጋገራቸው የከተማዋ ነዋሪዎች መካከል ሻምበል አይናለም ሽብሩ የመሪዎቻችንን ብሩህ ተስፋ በመከተል የተተከሉ ችግኞችን በመንከባከብና በሌሎች የልማት ዘርፎች ተሳትፎአችንን በማጎልበት የበኩላችንን ድርሻ እንወጣለን ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይ ህዝብ በእንቢተኝነት ትውልዱን ከእልቂት ሊታደግ ይገባል!

የትግራይ ህዝብ እንደ የትኛውም የሀገሪቱ ህዝብ የራሱን እጣ ፈንታ በራሱ የመወሰን ፍጥረታዊም ሆነ ፖለቲካዊ መብት አለው። ይህንን መብቱን ለማስከበርም የማንንም ሞግዚትነት የማይፈልግ ፤ ለዘመናት የዳበረ መንፈሳዊ ፣ማህበራዊ ፣ባህላዊ እና ፖለቲካዊ እሴቶች ባለቤት ነው።

በሀገረ መንግስት ግንባታ ውስጥ ሰፊ ድርሻ ያለው፣ ሀገርን ከውጪ ጠላት በመከላከል ተጋድሎ ውስጥም ጎልቶ የሚጠቀስ፣ በኢትዮጵያዊ እሴቶች የተገነባ፣ ለፍትህና ነጻነት ቀናኢ፣ በኢትዮጵያዊነቱ ተደራድሮ የማያውቅ፣ በኢትዮጵያዊነቱም ኩሩ የሆነ ህዝብ ነው ።

ለፍትህና ለነጻነት ካለው ቀናኢነት አንጻር ባለፉት አምስት አስርት አመታት ራሱን ከፍ ላሉ ችግሮች ባጋለጡ ታሪካዊ ክስተቶች ውስጥ ለማለፍ የተገደደ ህዝብ ነው። በዚህም የከፈለውም ሆነ እየከፈለ ያለው ዋጋ በህዝቡ የቅርብ ሆነ የሩቅ ጊዜ ታሪክ ውስጥ አቻ ሊገኝለት የሚችል አይደለም።

የህዝቡን የለውጥ፣ የፍትህና የነጻነት መሻት መሰረት አድርጎ በአዲስ አበባ ተጸንሶ በደደቢት በረሃዎች የተወለደው አሸባሪው ህወሓት የህዝቡን መሻት የፖለቲካ መቆመሪያ፣ የእድል ካርድ አድርጎ በመጠቀም የትግራይን ህዝብ በነጻነት ትግል ስም ከፍ ያለ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል አድርጎታል።

ቡድኑ በተሳሳተ የትግል ስትራቴጂ በሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣቶችን ለህልፈት፣ በመቶ ሺ የሚቆጠሩትን ለአካል ጎዶሎነት ዳርጓል። የትግራይ እናቶች ልብ በሀዘን እንዲሰበር ከማድረግ አልፎ ቀጣይ ተስፋቸው በጽልመት የተጋረደ እንዲሆን፣ ያለ ጧሪ ቀባሪ፣ አይዞሽ ባይ እንዲቀሩ አድርጓል።

ብዙ ከተባለለት የነጻነት ትግል ማግስትም የትግራይ እናቶች ከመርዶ ውጪ ያተረፉት አልነበረም ፤ብዙ የተዘመረለት ፍትህና ነጻነትም በትግሉ ወቅት ብዙ ዋጋ ለከፈሉት እንኳን ባእድ ሆኖ ሀገርና ህዝብ ለአዲስ አምባገነናዊ ስርአት ለተዳረጉበት ታሪካዊ ክስተት ምንጭ ሆኗል።

የትግራይ ህዝብም እንደ ህዝብ በብዙ ተስፋ ለትግሉ ከፍ ያለ መስዋእትነት ቢከፍልም በስርአት ደረጃ እንደ አዲስ የበቀለው የህወሓት አምባገነናዊ ስርአት ሰለባ ሆኗል። የራሱን እጣ ፈንታ በራሱ የመወሰን ፍጥረታዊም ሆነ ፖለቲካዊ መብት ተነፍጎ በቡድኑ እስትንፋስ እንዲኖር ተገዷል ።

በገዛ ልጆቹ የመስዋእትነት ደም ነፃነቱን ተነፍጎ ፣ለነፃነት ባይተዋር የሆነበትን ኖር እንዲኖር ተገዷል። በራሱ ስለ ራሱ እጣ ፈንታ ማሰብ የማይችል እስኪመስል ከሀይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቹ ባፈነገጠ መንገድ ሕይወቱን እንዲመራ ተደርጓል፤ በዚህም እያስተናገደ ያለው ማህበራዊ ምስቅልቅል ከአቅሙ በላይ ሆኗል።

በልጆቹ አስተዳደግም ሆነ ቀጣይ ሕይወት ላይ እንደ ቤተሰብ የመወሰን ፍጥረታዊ አቅሙን ተነጥቆ፣ ልጆቹ የሽብር ቡድኑ የአመጽ እቃ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ የህዝቡን ነገዎች ሊዋጁ ለማይችሉ ያረጁ ያፈጁ ቆሞ ቀር አስተሳሰቦች አቅም መግዣ ሸቀጥ ሆነዋል። ለዚህም በልጆቻቸው ምክንያት ቁም ስቅላቸውን የሚያዩ የትግራይ ወላጆች ተጨባጭ ማሳያ ናቸው ።

ይህ ሁሉ በነጻነት ስም በትግራይ ህዝብ ላይ የተጫነ ቀንበር ሊሰበር የሚችለው በከንቱና ተራ ፕሮፓጋንዳ ተወናብዶ በራሱ እና በትውልዱ ላይ የቡድኑን ቀንበር የጫነው ራሱ የትግራይ ህዝብ ነቅቶ፤ የችግሩን ባለቤት አውቆ በቃ ሲል ብቻ ነው ። ለዚህ ደግሞ ሊፈጥን ጊዜ ላያባክን ይገባል።

አሁን ላይ ቡድኑ በትግራይ ወጣቶች ደም ለአመታት የሰራቸውን ግፎች ለማወራረድ እየሄደበት ያለው የጥፋት መንገድ ከመቼውም ጊዜ በላይ የትግራይን ህዝብ በተለይም ደግሞ የትግራይን ወጣት ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ለስሌት የሚመች አይሆንም። ለዚህ እውነት ፈጥኖ መንቃትና እምቢተኛ መሆን ያስፈልጋል ።

የትግራይ ህዝብ ከህወሓት ፖለቲከኞች ተራ ዲስኩር ፣ ከአክቲቪስቶች ሆይ ሆይታ ፤ ከካድሬዎች ጫጫታ ወጥቶ አሁናዊ እውነታውን ከትናንት የቡድኑ ታሪክ ጋር በማነጻጸር በህዝባዊ እንቢተኝነት ትውልዱን ከእልቂት ሊታደግ፣ ልጆቹ ብዙ ዋጋ ከፍለው ያለፉበትን ነጻነቱን በእጁ ሊያስገባ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የትግራይ ወጣት የተፈጠረው ለጥይት ሳይሆን ከፍ ላለ ሰብአዊ አላማና ተልእኮ ነው!

ከመርደ ጽዮስ

በትግራይ ወጣቶች ደምና በትግራይ ህዝብ ተስፋ በመቆመር ዘመኑን የፈጀውና ዛሬም እየቆመረ ያለው አሸባሪው ህወሀት ከትናንት ስህተቱ መማር የሚያስችለውን እድል እየገፋ የመጨረሻ እስትንፋሱ የሚቋረጥበትን የጥፋት መንገድ ሊገፋበት ዳር ዳር እያለ ይገኛል።

በደደቢት በረሀ ተወልዶ በክፋት እና በሴራ አድጎ ፤ በንጹሀን ደም ገዝፎና ደልቦ በእብሪትና በማን አለብኝነት መንፈስ ላለፉት 50 አመታት ሀገርና ህዝብን ፤ በተለይ ደግሞ የትግራን ህዝብ ከፍ ያለ ዋጋ አስከፍሏል ።የትግራይን ምድር የደም ምድር ከማድረግ ጀምሮ ህዝቡን የጉስቁልና መገለጫ እንዲሆን አድርጎታል ።

ቡድኑ ለ17 አመታት በፍትህና ነጻነት ስም ባካሄደው ደም አፋሳሽ ጦርነት የትግራይን ወጣት በርካሽ ፕሮፖጋንዳ በማነሳሳት መሳሪያ አሸክሞ የበረሀ ሲሳይ አድርጓል፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩትን ለአካል ጉዳተኝነትና ለስነልቦና ቀውስ ዳርጓል። በክልሉ የትኛውም አይነት የልማት ስራዎች እንዳይካሄዱ እንቅፋት ከመሆን ጀምሮ ህዝቡ የተረጋጋ ህይወት እንዳይኖረው በማድረግ ለጀመረው ጦርነት አቅም አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል ።

ወጣቱ በየትኛውም መንገድ ተስፋ የሚቆርጥበትን ሁኔታ በማመቻቸት፤ ይህንኑ የወጣቱን ተስፋ መቁረጥ የፖለቲካ ቁማር መቆመሪያ የእድል ካርድ እና የጥፋት መንገዱ አቅም አድርጎ ተጠቅሟል። ከዚህም ባለፈ በረሀብ አደጋ ውስጥ የነበሩ፤ በሞትና በህይወት መካከል ጣር ውስጥ ለሚኖሩ የክልሉ ነዋሪዎች ሲቀርቡ የነበሩ የእርዳታ አቅርቦቶችን በመሸጥ ፍጹም ኢ-ሰብአዊ ተግባር የመፈጸም ጸያፍ ታሪክ ባለቤትም ነው ።

ከተጠናወተው የመስፋፋት እብደት የተነሳም በወልቃይትና በራያ አማሮች ላይ ያካሄደው የዘር ማጥፋትን ጨምሮ የተለያዩ አሰቃቂ ወንጀሎች ቡድኑ የቱን ያህል ሰብአዊነት የሌለው፤ ለህዝብና ለህዝባዊነት የተገዛ የአስተሳሰብ መሰረት እንደሌለው በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

በብዙ ርካሽ ፕሮፖጋንዳ በበረሀ ትግል ያሰለፋቸውን፤ በትግሉ ዘመናቸውን የከፈሉ ታጋዮችንና አመራሮችን ሳይቀር በድል ማግስት በብዙ ማዋረድ እና ስም ማጥፋት ሲያባርር ሁለቴ ማሰብ ያልቻለ የጥቂቶች ፈላጭ ቆራጭነት የተንሰራፋበት፤ የነዚህ ግለሰቦች ነውር የነገሰበት ድርጅት ነው።

ነውርን እንደ ነውር ከማየት ይልቅ ትምክህት አድርጎ የማየት ባህል ያዳበረ ፤ ከነውሮች በስተጀርባ የሚፈጠረውን የማህበረሰብ የህይወት ዝብርቅርቅ እንደ ስኬት በመቁጠር የሚኮፈስና፤ ይህንንም ለማስቀጠል የሚተጋ የነውሮች ሁሉ አባት ነው ።አምጦ የሚወልደውም ይህንኑ ነውሩን ነው።

“ሀገር ለማፍረስ እስከ ሲኦል እንወርዳለን” ከሚለው የአደባባይ ዲስኩሩ አንስቶ ፤በተግባር የተለያዩ ቡድኖችን አስታጥቆ ንፁሀንን በአሰቃቂ ሁኔታ ማስገደልን እንደ አንድ የፖለቲካ ስኬት የማየቱ እውነታ የዚሁ ማንነቱ መገለጫ ነው ። የትግራይን ህዝብ ለመጠበቅ ለሃያ አመታት በቀበሮ ጉድጓድ በነበረው የመከላከያ ሰራዊት ላይ ከኋላ ያደረሰው ጥቃትና ጥቃቱን ተከትሎ ያሰማው ፉከራና ቀረርቶ የዚህ ነውሩ ጥግ ነው ።

በህዝባዊ አመፅ ያጣውን ስልጣን በለመደው መንገድ በትግራይ ወጣቶች ደም ዳግም በእጁ ለማስገባት የሄደበት የእብሪት መንገድ ሀገርና ህዝብን ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፈለና እያስከፈለ ቢሆንም፤ በቡድኑ የእብሪት ድርጊት ከትግራይ ህዝብ በላይ ለከፋ ችግር የተዳረገ የለም ።ህዝቡ በአንድ በኩል ቡድኑ በለኮሰው ጦርነት ለነገው ተስፋ ያደረጋቸውን በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ወጣቶቹን አጥቷል ።

ከዚህም በተጨማሪ ከጦርነቱ ማግስት ጀምሮ ውስብስብ ለሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተዳርጓል ።ለዘመናት አብሯቸው በሰላምና በፍቅር ከኖራቸው አጎራባች ህዝቦች ጋር እንዲቃቃር ሆኗል።ይህም አጠቃላይ በሆነው የህዝቡ የእለት ተእለት ህይወት ላይ ያልተገባ ሸከም ይዞበት መጥቷል። በዚህም እየከፈለ ያለው ዋጋ ከፍያለ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ይህ ሁሉ እየሆነ ባለበት እውነታ ውስጥ ዛሬም ቢሆን ይህ አሻባሪ ቡድን በሱ እብሪትና ነውር ምክንያት የትግራይ ህዝብ እየከፈለ ያለውን ያልተገባ ዋጋ ለመመልከትና እራሱን እየሄደበት ካለበት የጥፋት መንገድ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም። ከዚህ ይልቅ በለመደው ተራ የማደናገሪያና የማደንዘዣ ፕሮፓጋንዳ ዳግም የትግራይን ወጣት ለእልቂት እያነሳሳ ይገኛል ።

በአንድ በኩል አለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማሳሳት መንግስት የዘረጋውን የሰላም እጅ ተቀብያለሁ እያለ፤ ስለ ሰላም ከባህሪው ጋር የማይሄዱ ዜማዎችን እያዜመ በሌላ በኩል ቅደመ ሁኔታዎችን ከመደርደር አንስቶ መላው የትግራይ ወጣት በግድም ይሁን በውድ ለጦርነት እንዲዘጋጅ እያደረገ ይገኛል ።

ላለፉት አራት አመታት የትግራይን ህዝብ እንደ ህዝብ በመያዣነት እየተጠቀመ ያለው አሸባሪው ሕወሀት፤ የትግራይን ህዝብ ሕይወት ስራዬ ብሎ በማመሰቃቀል ለእኩይ አላማው ግብአት እያደረገ ሲሆን ፤ በተለይም ወጣቱ የህይወት ጭላንጭል ተስፋ እንዳይኖረው በማድረግ መሳሪያ ማስታጠቁንና ለጦርነት ማዘጋጀቱን ገፍቶበታል ።

ይህ ከቀደመው ባህሪው የሚቀዳው የቡድኑ እኩይ ተግባር ዛሬ ላይ የትግራይን ህዝብ ሊያስከፍለው የሚችለው ዋጋ ከቀደመው ዘመን ጋር ሊወዳደር የሚችል አይሆንም ። ፍጻሜውም የቡድኑ አእምሮ ቢስ አመራሮች እንደሚያስቡት ሳይሆን፤ ድንገትም የቡድኑን ግብአተ መሬት የሚያፋጥን እንደሚሆን መገመት የሚከብድ አይሆንም ።

ይህንን ሀገራዊና አካባቢያዊ እውነታ የትግራይ ህዝብ፤ በተለይም የትግራይ ወጣቶች በአግባቡ ሊያጤኑት ያስፈልጋል። ትናንት ወንድሞቻቸው በፍትህና በነጻነት ስም የከፈሉት መሰዋእትነትና ያሳለፉት መራራ ሕይወት ለትግራይ ህዝብ ምን አመጣለት ብለው ሊጠይቁ ይገባል።

ቡድኑ በስልጣን ላይ በነበረባቸው 27 አመታት የትግራይ ህዝብ በሴፍቲ ኔት ፕሮግራም በሚታደል ስንዴ ህይወቱን ከመምራት ፤ በተለያዩ አደረጃጀቶች ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶችን ከማጣት ውጪ ምን አተረፈ ? ልጆቹስ ከስደትና ስደት ከፈጠረው ሞት ውጪ ምን ተፈጠረላቸው ? የትግራይ ወጣቶች ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል ።

ጠበንጃ ታጥቆ ቃታ ለመሳብ ከመሽቀዳደም በፊት ቃታ የምትስብበት ሀይል በርግጥ ጠላት መሆኑንም ማረጋገጥ ያስፈልጋል ፤በጠላትህ ነው ትርክት የሚሳብ ቃታ አደጋውና መዘዙ ብዙ እንደሆነም ማሰብ ተገቢ ነው። የትግራይን ህዝብ ከ10 አመት በላይ በቀበሮ ጉድጓድ ሆኖ ሲጠብቅ የነበረ ሀይል ላይ ቀደም ሲል የተሳበው ቃታ ምን ይዞ እንደመጣ አሁን ላይ ማስታወስ አዋቂነት ነው ።

በዘፈንና በተራ የሆይሆይታ ፕሮፓጋንዳ ታጥኖ ወደ ጦርነት የሚደረግ ጉዞ ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ከፍ ያለ ነው ።ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንጻር የትግራይ ወጣቶች እንደ ትናንቱ ዛሬም በደሙ እየቆመሩ ላሉ የህወሀት የአእምሮ ደናግልት በቃችሁ ሊሉቸው ይገባል።የትግራይ ወጣት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን የተፈጥሮ ጸጋ ባለቤት እንደሆነ ከፍ ባለ ድምጽ ሊያሰማቸው ይገባል ። የተፈጠረው ለጥይት ሳይሆን ከፍ ላለ ሰብአዊ አላማና ተልእኮ መሆኑን በእምቢታ ሊያሳውቃቸው ጊዜው አልረፈደም! ።

## ነፃ ሃሳብ

# እንጠይቅ... ለጥያቄያችንም መልስ እንፈልግ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አለም በመጠየቅ ፍልስፍና ውስጥ ናት:: እውነት የት ነው ብሎ መጠየቅ የአንድ ማህበረሰብ ህዳሴ መሰረት ነው:: ሀገር በጥያቄ ስትገነባና በአሉባልታ ስትገነባ ሁለት አይነት ናት:: በጥያቄ የተገነባ ሀገር በአሉባልታ አይፈርስም:: በአሉባልታ የተገነባ ሀገር ግን በምንም ለመፍረስ ቅርብ ነው:: የድሮዋ ኢትዮጵያ እውነትና ፍቅር አንድነትም ያቆሟት የመጠየቅ ውጤት ነበረች:: የአሁኗ ኢትዮጵያ ግን የአሉባልታ ውጤት የመሆን አደጋ ውስጥ ነች:: በተለይ ባለፉት ሀምሳ አመታት ውስጥ ያልሰማነው የውሸት አሉባልታ የለም:: ዛሬ ላይ እያገፋፉን ያሉት እነዛ አሉባልታዎች ናቸው:: ዛሬ ላይ እያቀያየሙን ያሉት ያልጠየቅናቸው ጠይቀንም መልስ ያላገኘንባቸው ችግሮቻችን ናቸው::

የህዝቡን ስነ ልቦና የተረዱ አንዳንድ ራስ ወዳድ ግለሰቦች መልስ የሌለው ጥያቄ እየፈጠሩ ሀገራችንን ሲያስጨንቁ ኖረዋል:: ያልሆነና ያልተደረገ ነገር እንደሆነና እንደተደረገ በማስመሰል ህዝብ የሚያባሉ ጥቂቶች አይደሉም:: ህዝብ ካልጠየቀና ለጥያቄዎቹ መልስ ካላገኘ ትውልዱ ተጠራጣሪ መሆኑ የማይቀር ነው:: ተጠራጣሪ ትውልድ ደግሞ ለነገ የሚሆን ቀርቶ ለዛሬ የሚሆን ታሪክ ለመስራት የሚሆን ቁመና የለውም፤ አይኖረውምም:: ሳንጠይቅ ያለውንና የሰማውን ዝም ብሎ ተቀብሎ የሚሄድ ትውልድ የጥቂት ፖለቲከኞችና፣ ራስ ወዳድ ቡድኖች መጫወቻ መሆኑ የማይቀር ነው ::

ሀገርን በጥያቄ ውስጥ መፈለግ ችግሮችን በዘላቂነት ለማፈላለግ ወሳኝ አቅም ነው:: እኛም በችግሮቻችን ዙሪያ የመጠየቅ ባህል አዳብረን ቢሆን ኖሮ ችግሮቻችን በዚህ ልክ ስር ሰደው ግራ ባላጋቡን ነበር:: አንድ ነገር ሲፈጠር እውነት ነው ብለን ከመቀበላችንና ለውሳኔ ከመነሳታችን በፊት ስለችግሩ ማወቅና በቂ መረጃ ማግኘት ያሻናል:: ስሜታዊነት ሀገር አይገነባም:: የሀገር ልዕልና ያለው በሰከነ አእምሮና ልብ ውስጥ ነው:: የእስከዛሬ ችግሮቻችንን ዛሬ ላይ ያን ያክል ጥፋትና ውድመት ባላስከተሉ ነበር::

እኛ ከማድመጥ ይልቅ ለመናገር፣ ከመጠየቅ ይልቅ በለው፣ አሳደው የሚቀናን ነን:: ችግሮቻችን ከጎዱንና ብዙ ነገር ካሳጡን በኋላ የምንነቃ ነን:: የሰው ልጅ ከትላንቱ ካልተማረ ለራሱም ሆነ በዙሪያው ላሉ የሚጠቅመው አንዳች የለም:: እኛ ደግሞ የሚያስተምሩን ብቻ ሳይሆኑ ደም እንባ ያስለቀሱን ትላንትናዎች ያሉን ህዝቦች ነን:: ትላንትን ገሎ መቅበር ያቃተን የትላንት ባሪያዎች ነን:: ሰው እንዴት በትላንት ጥፋት ደጋግሞ ይሞታል? ሰው እንዴት አምናን እያስታወሰ ደጋግሞ ይሰቃያል:: ለዛውም ውሸታሞች በፈጠሩት የማስመሰል ድራማ፣ ለዛውም መሰረት በሌለው የፖለቲካ ጨዋታ:: እንጠይቅ..ወደ ከፍታ የሚወስደን፣ ወደ አንድነት የሚያደርሰን የእድገት ጎዳና የቱ እንደሆነ እንመርምር:: እንጠይቅ...አለም የተለወጠበት የስልጣኔ መርህ የቱ እንደሆነ እንድረስበት::

በዘመን ሀዲድ ላይ እስኪበቃን ተራምደናል:: ፊተኞች ተብለን፣ የነጻነት ምድር ተብለን አለም አውቆናል:: ግን ዛሬም ድረስ በጥንቱ ታሪክ የምንጠራ ነን:: ዛሬም ድረስ በአባቶቻችን ትውፊትና ስልጣኔ ላይ የቆምን ነን:: የራሳችንን ኢትዮጵያ መገንባት አልቻልንም:: የራሳችንን ታሪክ፣ የራሳችንን እውነት መጻፍ አልቻልንም:: ኋለኞች ፊተኞች ሆነው በእኛ ላይ ሀይልና ክንዳቸውን ሲያሳዩን እያየን ነው:: በአባቶቻችን የተፈጠሩ፣ በእኛ ስልጣኔ ቀን የወጡ ሀገራትና መንግስታት ዛሬ ላይ በእኛ ላይ የበላይ ሆነው ካልዳኘናችሁ እያሉን ነው:: ይሄ አያሳፍርም ትላላችሁ? ።

ኢትዮጵያ ጸንሳ የወለደቻቸው የአፍሪካ ሀገራት፣ በአባቶቻችን የደመቁ የአለም ሀገራት ዛሬ እኛን ከኋላ አስከትለው በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በስልጣኔ እናውቅላችኋለን ሲሉን ከዚህ በላይ ምን ውርደት አለ? እንጠይቅ..ጠይቀንም መልስ እናግኝ:: ኢትዮጵያችን በፍቅር ማጣት እየተንሳቀለች ነው:: ኢትዮጵያችን በወንድማማቾች መካከል በሚፈጠር ጦርነት፣ በሚፈጠር የፖለቲካ ቁርሾ እየተንገዳገደች ነው:: በተባበረ ክንድ ታሪክ መስራት ተስኖናል:: ይሄን የመለያየት ካባ ማን እንዳለበሰን፣ ፍቅር በሌለው የመለያየት ቤት ውስጥ እንድንቆም ማን እንደፈረደብን እንጠይቅ:: በጠዋት ተነስተን ለፍቅር የሚረፍድብን፣ በጎህ ነቅተን ለይቅርታ የሚመሽብን ምን ስለሆንን ነው ስንል እንጠይቅ::

ለጥያቄዎቻችንም በጋራ መልስ እንፈልግ:: ሀገር ምክክር ላይ ናት:: ሀገር በእርቅና በተግባቦት ከፍ ለማለት ከህዝቦቿ ጋር እየሰራች ነው:: ሁላችንም የተሳተፍንበት፣ ሁላችንንም የሚያግባባ፣ ወደ ፍቅር የሚወስደን በመጠየቅ የተገኘ የላቀ እውነት ያስፈልገናል:: ከዚህ በኋላ ባለመጠየቅ ሲያሰቃዩን የነበሩ ችግሮቻችንን ነጠላ በማዘቅዘቅ አልቅሰን ቀብረን ዳግም ታሪኮቻችን የማይበላሹበትን፣ ኢትዮጵያችን የማታዝንበትን፣ ትውልዱ የማይመረዝበትን የጋራ ፖለቲካ መፍጠር አለብን:: ባለመነጋገር ለዘመናት ሲያባሉን የነበሩ ፖለቲካዊም ሆኑ ማህበራዊ ችግሮቻችንን ሳይንሳዊ በሆነ በተጠና አካሄድ አሸንፈን ቀና የምንልበትን የእፎይታ ጊዜ መፍጠር አለብን::

> **ዛሬ ላይ ጥሩ ሀገር መፍጠር ያልቻልነው ጥሩ ጥያቄ ስለሌለን ነው፡፡ ጥሩ ህዝብና ጥሩ ትውልድ መፍጠር የተሳነን ደግሞ በጥያቄ የተፈጠረች ሀገር ስለሌለችን ነው፡፡ ጥሩ ጥያቄዎች ሁሌም ጥሩ መልስ አላቸው፡፡ ጥሩ ጥያቄዎች ጥሩ ሀገርና ጥሩ ትውልድ ለመፍጠር መሰረት ናቸው**

በዚህ የጋራ እውነት ውስጥ ካላለፍን "ውሀ ቢወቅጡት እንቦጭ "እንደተባለው መልሰን መላልሰን ያው ከመሆን ውጪ የምናመጣው ለውጥ አይኖርም:: መጀመሪያ በመጠየቅ ጥበብ የችግሮቻችንን መነሻ ምክንያት ፈልገን እናግኝ:: ከዛ በኋላ እዳው ገብስ ነው፤ መነሻው የታወቀ ነገር ሁሉ መድረሻ አለው:: እኛም ያን በመጠየቅ ያገኘነውን የችግራችንን መነሻ ይዘን በምክክርና በሀገራዊ እርቅ ወደፍጻሜው እንሄዳለን:: ችግር የሆነብን ሳንጠይቅና ማህበረሰቡን ሳናወያይ መነሻ ምንጩንም ሳናውቅ ለመፍትሄ መቀመጣችን ነው:: ምንጩ ያልታወቀ ችግር መፍትሄ የለውም:: ሁሉም ነገር በምክንያትና ውጤት ውስጥ የሚያልፍ ነው:: ውጤት ካለ ምክንያት አለ:: ምክንያት ካለ ውጤት ግድ ነው:: እኛም የችግሮቻችንን ማብቂያ ለማወቅ መነሻ ምክንያታቸውን ማወቅ ግድ ይለናል::

ሀገር መፍጠር ጀግና መፍጠር ነው:: ሀገር መፍጠር ታሪክ መፍጠር ነው:: እኛም በመጠየቅና ጠይቆ መልስ በማግኘት መጪው ትውልድ የሚኮራበትን ሀገርና ታሪክ መፍጠር ይጠበቅብናል:: በዜጎች በጥያቄ የተፈጠረች ሀገር እጣ ፈንታዋ ስልጣኔና ፊተኝነት ነው:: በዜጎች ጥያቄና መልስ የተፈጠረ ማህበረሰብ ፍቅርንና አንድነትን መርህ አድርጎ ከመኖር ባለፈ አማራጭ አይኖረውም:: ከዚህ እውነት በመነሳት የእኛ ሀገር ምን እንደነበረች መረዳት እንችላለን:: የእኛ ሀገር ዜጎች ጥያቄ አይጠይቁም፣ እንዲጠይቁም እድል አይሰጣቸውም::

በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ አብዛኛው የአለም ስልጡን ሀገራት መንግስት ለዜጎች በፈጠረው የመጠየቅ መብት የተፈቱ መሆናቸው ነው:: ጥሩ ጥያቄ ጥሩ ሀገር ይፈጥራል፤ ጥሩ መልስ ግን በጥሩ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ጥሩ ህዝቦችንና ጥሩ ትውልዶችን ይፈጥራል :: ዛሬ ላይ ጥሩ ሀገር መፍጠር ያልቻልነው ጥሩ ጥያቄ ስለሌለን ነው:: ጥሩ ህዝብና ጥሩ ትውልድ መፍጠር የተሳነን ደግሞ በጥያቄ የተፈጠረች ሀገር ስለሌለችን ነው:: ጥሩ ጥያቄዎች ሁሌም ጥሩ መልስ አላቸው:: ጥሩ ጥያቄዎች ጥሩ ሀገርና ጥሩ ትውልድ ለመፍጠር መሰረት ናቸው::

ጥሩ ሀገር ለመፍጠር በጥያቄዎቻችንም ሆነ በመልሶቻችን ላይ እኩል ተሳታፊ መሆን ይኖርብናል:: የተወሰኑ ሰዎች እየጠየቁ የተወሰኑ ሰዎች የሚመልሱላት ሀገር የጋራ ታሪክ አይኖራትም:: የጋራ ሀገር፣ የጋራ ታሪክ፣ የጋራ እሴት እንዲኖረን በጋራ ጠይቀን በጋራ መልስ መፈለግ ይኖርብናል:: የሀገራዊ ምክክሩ ዋና አላማ ደግሞ ይሄ ነው:: በጋራ መክሮ፣ በጋራ መፍትሄ ማምጣት:: በጋራ ጠይቆ በጋራ መልስ መፈለግ:: በጋራ መክሮ፣ በጋራ ውሳኔ መወሰን ነው:: ሀገራችን የጋራችን እንደመሆኗ መጠን በጋራ መልፋት፣ በጋራ መድከም ይጠበቅብናል::

አንዱ እየለፋ፣ አንዱ ጉዳዩ አይደለም በሚል የምንአገባኝነት ስሜት የምትቆም ሀገር የለችንም:: ሀገራችን በጋራ አምጠን፣ በጋራ የምንወልዳት የጋራ ሀሳባችን ጽንስ ናት:: ጥሩ ሀገር ለመውለድ ጥሩ ሀሳብ ማማጥ ይኖርብናል:: ጥሩ ትውልድ ወልዶ ለማሳደግ ጥሩ ዘር መዝራት ይጠበቅብናል:: ዘራችን ሀሳባችን ነው:: ዘራችን ፍቅር ነው:: ዘራችን ተነጋግሮ መስማማት ነው:: ክፍት በሆነ የምክክር መድረክ ችግሮቻችንን በጥያቄ እናሸንፍ:: ድህነታችንን በመፍትሄ እንርታ::

ካለጥያቄ፣ ካለመፍትሄ ዜጋ መሆን ብቻውን ትርጉም የለውም:: ዜግነት በሀገር ጉዳይ ላይ ከመጠየቅና ጠይቆም መልስ ከመስጠት የሚጀምር ነው:: ዜግነት በሀገር ጉዳይ ላይ ከመንግስት ጋርም ሆነ ከየትኛውም የማህበረሰብ ክፍል ጋር የሚወያይና የሚነጋገር ነው:: የልጅነት እውቀታችን የሚነግረን እኮ ህዝብ ማለት መንግስት፣ መንግስት ማለት ህዝብ ነው ሲል ነው:: ዜግነት ብዙ ቁጥር ሲሆን ህዝባዊነት፣ መንግስታዊነት ነው::

የእኛ ሀገር ዜግነት ግን አስቂኝ ነው..ምን አገባኝ፣ አይመለከተኝም በሚል አፍራሽ አመለካከት ተኮትኩቶ ያደገ ነው:: ዜግነታችንን ለሀገር በመልፋት፣ ለሀገር በማሰብ፣ ለሀገር በመቆርቆር መጀመር አለብን:: በሀገር ጉዳይ ላይ በመነጋገርና በመመካከር ዜግነታችንን ጥቅም ላይ ካላዋልነው እኛ ሞኞች ነን:: ምክንያቱም የምንፈልገው ሰላም፣ የምንፈልገው እድገት፣ የምንፈልገው ስልጣኔ ሁሉ በእኛ ጥያቄና መልስ ውስጥ የተደበቀ በመሆኑ ነው:: ካለፈው ይልቅ የሚመጣው ይበልጣልና ለድህነትና ለሰላም ማጣት የዳረጉንን ችግሮቻችንን በማሸነፍ አዲስ የመጠየቅና የመመካከር ልምድን የእኛ እናድርግ ::

ራሳችንን ለይቅርታና ለትዕግስት ሳናስገዛ ለውጥ የለም:: ራሳችንን ለጠንካራ የምክክር ልምድ ሳናበቃ ለውጥ የለም:: ራሳችንን በእውቀት ሳናጎለምስ ለውጥ የማይታሰብ ነው:: ጊዜው የእኛን ታማኝነት የሚጠይቅ ነው:: ኮሮና አለ፣ የኑሮ ውድነት አለ፣ የሰላም ማጣት አለ፣ የውጪ ጫናዎች አሉ በዚህ ሁሉ ውስጥ ሀገርን በታማኝነት ማገልገል የእውነተኛ ዜጋ መገለጫ ነው:: አንድን ሌባ ግለሰብ፣ ወይም አንድን ሙሰኛ ሰው፣ ወይም ደግሞ አንድን ነውጥ ፈጣሪ ወንበዴ ቤታችን ደብቀን ሌባ በዛ፣ አድሎ ተስፋፋ፣ መንግስት ህግ ማስከበር አልቻለም ብንል ልክ አይሆንም::

ልክ የሚሆነው ልክ የሆነ ነገር ብቻ ነው:: ልክ የሆነ ነገር ደግሞ ልክ በሆነ ስፍራ ላይ ነው የሚገኘው:: ሀገር በዜጎቿ ነው የምትጠበቀው:: የህግ የበላይነት ዋጋ የሚኖረው በዜጎች የያገባኛል መንፈስ ሲቃኝ ነው:: ህዝብ ወንጀልንና ወንጀለኛን ሲያጋልጥ፣ መንግስት ተገቢውን ቅጣት ሲሰጥ ያኔ ሁሉም ነገር ልክ መሆን ይጀምራል:: መጀመሪያ በቤታችን፣ በአካባቢያችን ያሉ ችግሮችን እንመልከት:: ጥያቄዎቻችን ሰላም ከሆነ መጀመሪያ እኛ ሰላም ወዳድና ሰላም ፈጣሪዎች እንሁን::

ጥያቄዎቻችን ልማት ከሆኑ ደግሞ መጀመሪያ በልማት የተጉ፣ በምክንያት የዳበሩ አእምሮን የእኛ ማድረግ ይጠበቅብናል:: ጥያቄአችን እድገት፣ ብልጽግና ከሆነ ደግሞ መጀመሪያ እጆቻችንን ለስራ መዘርጋት ግድ ይለናል:: ካለእኛ ተሳትፎ፣ ካለእኛ ሀላፊነት፣ ካለእኛ ትጋት መንግስት ብቻውን ምንም ማድረግ አይችልም:: መንግስት እንዲሰራም ሆነ እንዲቦዝን የሚያደርገው የዜጎች ጥያቄና የያገባኛል መንፈስ ነው::

ልክ የሆነ ነገር ያለው በመጠየቅ ውስጥ ነው:: ሳንጠይቅና ሳንመካከር ሀገራችንን ልክ ባልሆነ ስፍራ ላይ ያለክብሯ አስቀምጠናት ኖረናል:: አሁን ግን እንጠይቅ..ጠይቀንም መልስ እናግኝ:: ሰላሞቻችንን በመጠየቅ እንመልስ፣ አንድነታችንን በውይይት እናምጣ:: እስከዛሬ ያልሄድንባቸውን የልዕልና ጎዳናዎች በፍቅር እንሂድባቸው:: እነዛን ሳናውቅ ሲያገፋፉን የነበሩትን ፖለቲካ ወለድ አሉባልታዎች በይቅርታ እንሻገራቸው:: ከማይገባን ወጥተን ወደሚገባን ስፍራ ከፍ እንበል:: እንጠይቅ..ጠይቀንም መልስ እንፈልግ::

# ባህል ያጸናው የነጻነት እሴት

ጽጌረዳ ጫንያለው

ብዙ ሰዎች ነጻነት የሚለውን ቃል ከፖለቲካዊ አውድ ጋር ብቻ ያቆራኙታል። ሲተነትኑትም የሚታየው ከዚሁ አኳያ ነው። ይህ ትክክል አይደለም! ነጻነት የሚለውን ቃል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊም ጭምር ነው። እንደ አውዶቹ ገብቶ ጥምረቱን የሚያሳይም ነው። ምክንያቱም ነጻነት የሚለው ቃል የሰው ልጅ ባለበት ሁሉ ሊነሳ የሚችል ጉዳይ ስለሆነ። ስለነጻነት ሲነሳ ከሰዎች አዕምሮ በርካታ ጥያቄዎች ይሰነዘራሉ። ይኸውም ነጻነት ማለት ምን ማለት ነው? ፣ የት እና መቼ መተግበር ተጀመረ ? የሚሉት ጥያቄዎች መሰረታዊ ናቸው።

ከዚህ አንጻር ነጻነት ስለተባለው ጽንሰ ሃሳብ ማደግ እና መጎልበት ኢትዮጵያውያን ምንም አይነት አስተዋጾ እንደሌላቸው ሊናገሩ እና ሊጽፉ የሚዳዳቸው አሉ። ነገር ግን በተለይም ከባህላዊ ክንዋኔዎች ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያዊያን ልክ ነጻነትን የሰበከ አለ ለማለት ያስቸግራል። የአለም አገራት ጭምር ይህንን ይመሰክራሉም።

ኢትዮጵያዊያን ለልጆቻው ስለነጻነትን የሚያስተምሩት ገና ከልጅነት ጀምሮ መሆኑ ደግሞ አንዱ ነው። እንዴውም የኢትዮጵያ ህጻናት አፋቸውን የሚፈቱት ስለነጻነት እያወሩ እና እየተጫወቱ እንደሆነ የቡሔ በዓልን ብቻ በመጥቀስ መናገር ይቻላል። ከዚያም በኋላ ለሴቶች የነጻነት ገጸ በረከትን ይዞ ብቅ ያለው የነሐሴ ወር ስጦታም አንዱ ነው። እናም እነኝህ የደስታ በዓላትን ስናነሳቸው እንዲሁ ጨዋታ ብቻ አድርገን አይደለም! በባህላዊ ህግ እና በስርዓት የሚመሩ የነጻነት ቀን ማስተማሪያዎች እንጂ።

የሃገራችን ልጆች ነጻነትን «ሀ፣ሁ» ብለው የሚጀምሩበት ትምህርትቤት ሳይገቡ ነው። የመጀመሪያው የነጻነት ትምህርት ቤታቸውም ‹‹ቡሔ በሉ፤ ልጆች ሁሉ ›› እያሉ በሚያዜሙት ጨዋታ ነው። ይህ ሲሆን ደግሞ በሕግ እና ስርዓት ታጥረው ፤ የሃገራቸውን እሴትና ወግ ጠብቀውም ነው። በዚህም በሕግ የጸና እሴታችን ልጆችን ብቻ በስፋት እንዲያሳትፍ ተደርጎ መልካሙን የልጅነት ጊዜ በመልካም ስብዕና እያጎለበቱቱ እንዲሄዱ በማሰብ ቡሄ በሉ እያልን ሺህ ዓመታት አስቆጥረናል።

በዚህ ወቅት በስራ የተጠመደ ልጅ እንኳን ቢሆን ከመጫወት አይከለከልም። ምክንያቱም በዓሉ የእርሱ የነጻነት ቀን ነው። እናም ብዙ ሥራ እንኳን ቢኖር ሌላ ሰው እንዲሰራው ተደርጎ ከእኩዮቹ ጋር በመሆን እንዲቦርቅ በነጻ ይለቀቃል። ይህ እለት የደስታና የፌሽታ ቀን በመሆኑም የፈለገውን እያደረገ ይውላል። ከትርጓሜው ብንነሳ ቡሔ ማለት በራ፣ ብርሃን ሆነ፤ ደማቅ ፣ ገላጣ ሆነ ማለት ነው። እናም በዚህ ወቅት የክረምት ጨለማ አልፎ የብርሃ ወቅት ስለሚተካ ልጆች ችግር ይገጥማቸዋል ተብሎ አይታሰብምና ብሩሁን ቀን በለምለሙ ሜዳ ላይ እንዲያሳልፉ እድሉ ይሰጣቸዋል።

ቡሔ ሰማይ ከጭጋጋማነት ወደ ብሩህነት የሚለወጥበት የመሸጋገሪያ ጊዜ ስለሆነ ብራ ተብሎም ይጠራል። በዚህ ወቅት ነጻነታቸውን የሚያውጁት ልጆች ብቻ ሳሆኑ ወላጆችም ናቸው። ምክንያቱም ልጆችን ከመጠበቅ ያርፋሉ። እናም ‹‹ቡሄ ከዋለ የለምት ክረምት ፤ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት ›› ለእናትም ለልጅም ነጻነትና እረፍት ይሆናል ማለት ነው።

የቡሔ ሌላው የነጻነት ተምሳሌነት (ሊጥ ቡኮ) ከሚለው ስያሜው ጋር በተያዘ የሚመጣው ባህሪው ነው። በዚህ በዓል ቡኮ ተቦክቶ ሙልሙል ተጋግሮ የሚታደልበት በዓል ነው። እንደምታውቁት ዘመድም ሆነ አልሆነ የቡሔ ተብሎ በልጅ ልክ ዳቦ በየቤቱ ይወሰዳል። ትኩሱን ዳቦ መግመጥ ደግሞ ለልጆች ደስታን ይሰጣል። በእርግጥ የዚህ ስጦታ ምስጢር ሀይማኖታዊ ነው።

ጌታችን ብርሃነ መለኮቱን በገለጠበት ዕለት ጊዜው ምሽት ነበር። እረኞችም ከብርሃኑ የተነሣ እየተገረሙና እየተደነቁ ወደ ቤት አልተመለሱም። በዚህ ጊዜ የልጆቹ መዘግየት ያሳሰባቸው ወላጆች ችቦ አብርተውና ዳቦ ይዘው ፍለጋ ወጡ። ታዲያ ያንን ማስታወሻ አሁን ላይ «ቡሄ» ለሚሉ ልጆች ሙልሙል ዳቦ ይታደላል።

በዚህ የነጻነት ቀን ውስጥ ሌላዉ ልጆች እንዲተገብሩት የሚፈቀደውና ደስታን የሚፈጥረው ነገር ጅራፍ ማጮህ ነው። ስለዚህም በዓሉን ለማክበር ሲያስቡ ብዙ ጊዜ ተሰጥቷቸው የበዓሉ ቀን ከመድረሱ በፊት ዝግጅት ያደርጋሉ። ከመኖሪያ ቤታቸው ርቀውና በሜዳና በተራራማ አካባቢ ላይ ሆነው ጅራፍ ግርፊያ ጭምር ያደርጋሉ። የመወዳደር አቅማቸውን ያዳብራሉም።

በቡሄ ዕለት ልጆች በየእድሜ ክልላቸው ሆነው ለበዓሉ የተዘጋጀውን ሙልሙል ዳቦ በአገልግል ቋጥረዉ ከብቶቻቸውን ይዘው ወደ ሜዳ ይሄዳሉ። የያዙትን ሙልሙል ዳቦ በአንድ ላይ ተሰብስበው ይበላሉ። ከዚያም በኋላ " ቡሄ መጣ ያመላጣ ቅቤ ቀቡት እንዳይነጣ " እያሉ የየራሳቸውን ጅራፍ ያጮሃሉ። የጅራፍ ግርፊያም አንድ ለአንድ በመመራረጥ ያደርጋሉ። የቀን ውሎአቸውን በዚህ ካሳለፉ በኋላ አመሻሽ ላይ ከብቶቻቸውን ይዘው ሁሉም ወደየቤታቸው ይመለሳሉ። ማታ ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን ለበዓሉ የተዘጋጀው ዝግጅት ይታደማሉ።





ሁሉም የሰፈር ልጆችና አባቶች በአንድ ቦታ ተሰብስበው የችቦ ማብራት ስነ- ስርዓቱን ያከናውናሉ። አባቶች እየመረቁ ከዓመት ዓመት ያድርሰን እያሉ ልጆቹ ደግሞ ጅራፍ እያጮሁ ይቆያሉ። የችቦ ማብራት ስነ-ስርዓት ካበቃ በኋላ ተመራርቀው አባቶች ወደየቤታቸው ሲመለሱ ልጆች ግን በአንድ ላይ ተሰብስበው በየመንደሩ እየዞሩ" ሆያ ሆየ " እያሉ ይጨፍራሉ። ዳቦ ዋነኛ ስጦታ ሲሆን፤ አሁን አሁን ግን ነገሩ ተቀይሮ ብር ሆኗል። ግን ነጻነትን የማክበሩ ጉዳይ ሳይቀንስ የቀጠለ ነው።

ሌላው የቡሔ በዓል ለልጆች ነጻነትን የሰጠ እንደሆነ የምናረጋግጠበት ጉዳይ ‹‹በቡሔ ጨዋታ አይቆጡም ጌታ›› አይነቱ ተግባር ነው። ማለትም በጨዋታቸው ተደሰተም አልተደሰተም በሕግ የታሰረውን እሴት ያላከበረን ሰው በግጥሞቻቸው ይፌዝበታል። መቆጣት ደግሞ በምንም መልኩ አይቻልም። እናም ልጆች በነጻነት ትልቁ ሰው ጭምር ለምን አልሰጠኸንም በሚል ይሳለቁበታል። በዚያው ልክ ምንም ይሁን ምን ከተሰጣቸው ያሞግሳሉ። ያው በዛሬው ተቃራኒ ነገሮች ቢመጡም።

አባቶች ይህንን ቀን ሲመርጡት ሀይማኖታዊ ትርጉሙ እንዳለ ሁሉ ተፈጥሯዊም ግዳጅ አለው። አንዱ እንደ አገራችን ያለው የአየር ጠባይ ሲሆን፤ ዕለቱ ብራ የሚውልበት ስለሚሆን ምስራች ለመንገር ጥሩ ጊዜ እንደሆነ ያምናሉና መርጠውት ለልጆች ጊዜውን ሰጥተውታል። ተተኪነታቸውንም ለማብሰር የተጠቀሙበት እንደሆነም ይነገራል። ምክንያቱም የክረምቱ አፈና ተወግዶ የብርሃን ወገግታ ሲመጣ ደስተኛ ቤተሰብን ለመፍጠር ልጆችን ማስደሰት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ስለዚህም በየአካባቢው በገላጣው፤ ወገግታ በተፈጠረበት በብርሃኑ ወቅት ቡሔን እንደፈለጋቸው እንዲያከብሩት ፈቅደውላቸዋል።

ቡሄ በአብነት ተማሪዎች ዘንድም ትልቅ የነጻነት በዓል ነው። በዚህም ደብረ ታቦር ‘የተማሪዎች በዓል’ እየተባለ ይጠራል። ምክንያቱም በዚህ ወቅት ተማሪዎቹ ቀደም ብለው “ስለ ደብረ ታቦር" እያሉ ይለምኑና ደግሰው ማህበረሰቡን በመሰብሰብ ያበላሉ። ከቡሔ ወጣ ስንል የምናገኛቸው በነሃሴ ወር የሚከበሩ የሴቶች የነጻነት በዓላትን ነው።

ይህ በዓል በአማራ ክልል ሻደይ፤ አሸንድዬና ሶለን እንዲሁም እንግጫ ነቀላ እየተባለ ይከበራል። በትግራይ ደግሞ አሸንዳና ‹‹ዓይኒ ዋሪ›› እያሉ ያከብሩታል። በዳውሮ ዞን ደግሞ ወሩም ቢለይም ገዚያ እየተባለ በማህበረሰቡ ዘንድም ለሴቶች ነጻነት ክብር ተሰጥቶ በአደባባይ ያከብሩታል። ክብረ በዓሉ ሴቶችን ማዕከል ያደረገ፤ ለሴቶችና በሴቶችም የሚዘጋጅም ነው። እናም ነጻነት እንደ ኢትዮጵያዊያን ለልጆች ለሴቶች እየተባለ ጭምር የሚከፈልና የሚከበር እንደሆነ ከዚህ መረዳት ይቻላል። ለመሆኑ የሴቶች ነጻነት ቀንስ እንዴት ይከበራል ካላችሁ ትንሽ ሀሳብ እናንሳ።

በአማራ ክልል በየዓመቱ ከነሐሴ 14 ጀምሮ ይከበራል። በተለይም በሰቆጣ፣ በዋግምራ፤ በላሊበላና በቆቦ የመሳሰሉት አካባቢዎች ላይ በስፋት በድምቀት የሚከበርም ነው። ይህንን ሲያደርጉም ሴቶች በመንገዶችና አደባባዮች ላይ በመውጣት ነፃነታቸውን በማወጅ ሲሆን፤ ሴቶች ያለምንም ተፅእኖ ይጫወታሉም። በእርግጥ ነጻነታቸው የሚጀምረው በዓሉ ከመድረሱ በፊት ለዝግጅታቸው ከሚሰጠው ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚያ በተጨማሪም ቤተሰብ አልባሳትንና ጌጣጌጥን መግዛት አለያም ያላቸውን አጥበው መስጠት ይኖርበታል። ለሴቶች ብቻ ተብሎ የተተወውን የቤት ሥራ እንኳን ሌሎች እንዲከውኑት ይደረጋል። በቃ ሁሉ ነገር በእነርሱ ፍላጎት ብቻ ነው የሚከወነው።

ማንም መብታቸውን ሊጥስ ስለማይችል በዕለቱ ማንንም ሳይጠብቁ በራሳቸው የፈለጉትን ያደርጋሉም። የተነጠቀ ልጅነታቸው ጭምር የሚካሰው በዚህ ይሆናል። ስለዚህም የነጻነት ቀናቸውን ለማክበር ከሳምንት በፊት ጀምረው ይዘጋጃሉ። ይህ ሲሆንም የአንድ ሰፈር ሴቶች በመሰባሰብ፣ የሚለብሷቸውን አልባሳት በመምረጥ፣ ጌጣጌጦችን በመግዛትና በመጨረሻም ቡድኑን የሚያስተባብር አንድ ሰብሳቢም በመምረጥ ነው።

አከባበሩ የእድሜ እርከን የተቀመጠለት ሲሆን፤ እስከ 10 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች፤ ከ10 እስከ 15 ዓመት ድረስና ከ15 ዓመት በላይ የሚል ነው። መለያቸው ደግሞ ልዩ ልዩ ሲሆን፤ አለባበሳቸው፤ የጸጉር አሰራራቸውና መሰል ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። እንደውም በእዚህ ውስጥ የታጨችና ያልታጨች ጭምር ተብሎ ይታያል። ያገባችም እንዲሁ።

በዓሉ የነጻነት ጊዜ ነው ሲባል አንዱና ሌላው ማሳያው የወደፊት ኑሯቸውን መመልከቻ መድረክ ስለሆነም ነው። ማለትም ልጃገረዶቹ ለትዳራቸው የሚያጫቸው ሰው በግላጭ የሚያያቸው በዚህ የነጻነት በዓል ወቅት ነው። እንደውም በዚህ ጊዜ ሲጨፍሩ በቤተሰብ ባል ታጭቶላቸው ድፎ ዳቦና በግ ከአማቶቻቸው በእለቱ የሚመጣላቸውም አይጠፋም። ወንዶቹም የሚያጭዋትን ልጃገረድ በዚህ ጊዜ ይመርጣሉ ።

ሌላው ይህ ጊዜ የማመስገኛና ምርቃትን የመቀበያ ጊዜያቸው መሆኑም አንዱ ነው። ማለትም የነጻነታቸውን ቀን ለማክበር ሲነሱ ጉዟቸውን የሚጀምሩት ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ሲሆን፤ መልካሙን ሁሉ ከራሳቸው አልፈው ለአገር ለምድሩ ይለምናሉ። እንደሚሆንላቸውም ያምናሉ። ከዚያ በቀድሞው ጊዜ ወደ አካባቢው አስተዳደር ወይም አገረ ገዥው ነበር። አሁን ደግሞ በአካባቢው ትልቅ የሚባለው ሰው ጋር ጉዟቸውን አድርገው ምርቃታቸውን ይሸምታሉ። እንዲህ እንዲህ እያሉም ሰው ሳይመርጡ የተሰጣቸውን የነጻነት በዓል ያከብራሉ።

ይህ ጊዜ የተሰጥኦ መለያ ወቅታቸውም ነው። ምክንያቱም ድምጻ መረዋነታቸውን የሚሞከሩትና የሚያረጋግጡት በዚህ ቀን ነው። ለመዝፈን ያላቸውንም አቅም በዚህ ዕለት ያውቁታል። ስለዚህም የቀጣይ ሕልማቸውን ወደማመቻቸቱም ይገባሉ። እናም ‹‹አስገባኝ በረኛ፣ አስገባኝ ከልካይ፤ እመቤቴን ላይ›› በማለት ማንጎራጎር ይጀምሩና በመቀጠል ‹‹ይሄ የማን አዳራሽ የጌታዬ የድርብ ለባሽ፤ ይሄ የማን ደጅ የእመቤቴ የቀጭን ለባሽ›› በማለት እያሞገሱ ይዘልቃሉ።

በዚህ የነጻነት በዓል ወቅት ሰው አይለይም። ስለዚህም ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ነጻነት የሚታገሉበት ቀን እንዲሆን አድርገው ያሳልፉታል። ለዚህም ማሳያው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚኖረውን ሰው ሳይለዩ ማሞገሳቸው ነው። እንዲህ ሲሉም ያወድሱታል ‹‹አሸከር አበባዬ አሸከር አባብዬ (2) ይሙት፣ ይሙት ይላሉ የኔታ አሽከር አበባ አሽከር አይደለም ወይ የሚሆነው ጌታ››። ይቀጥሉናም ‹‹ከፈረስ አፍንጫ ይወጣል ትንኝ፤ እሰይ የኔ ጌታ ጤና ይስጥልኝ››፤ ‹‹ምድር ጭሬ፣ ጭሬ አወጣሁ ማሰሮ እሰይ የኔ እመቤት ድልድል ወይዘሮ›› ።

ሌላው የሴቶች የነጻነት ቀን ሲከበር ራሳቸውን ማስከበራቸው ተጠቃሽ ነው። እንዴት ከተባለ ዘፍነው ዘፍነው የሚሸልማቸው ካጡ ወይም ከዘገዩባቸው ዝም አለማለታቸው ሲሆን፤ በግጥማቸው መቃረናቸውን ያሳያሉ እንዲህ እያሉ « አንቱን አይደለም የማወሳሳው፤ ቀና ብለው እዩኝ የሰው ጡር አለው»።

የሰሜን ኢትዮጵያ የልጃገረዶች ጨዋታ ወይም የአደባባይ ክብረ በዓል በተለያዩ ባህላዊ ልብሶች በደመቁ ሴቶች ትውፊቱን ጠብቆ ለዘመናት ሲከበር የቆየውም ያለምክንያት አይደለም። ነጻነትን ለማለማመድ በሚደረገው ሩጫ ውስጥ የሴቶች ፍላጎት አይሎ በመውጣቱ ነው።

ከሰሜኑ ወጣ ስንል ደግሞ በደቡቡም የምናገኘው ነገር አለ። ወሩንም ሆነ የአከባበሩን ሥርዓት በመጠኑ ለየት ቢልም ተመሳስሎሹ ግን የሰፋ ነው። ምክንያቱም ይህ በዓል ጥቅምት ላይ የሚከበር ነው። በዳውሮ ዞን አዲስ ዓመት በገባ በሰባተኛ ሳምንት ማክሰኞ ላይ ይከበራልም። በሴቶች ብቻ በትልቅ ዛፍ ስር በድምቀት የሚከወንም ነው። የ‹‹ገዚያ›› እየተባለ ይጠራል።

በዚህ በዓል በሰሜኑ ክፍል እንደሚከበረው የነጻነት ቀን ተደርጎ ቢወሰድምና ሴቶች የፈለጋቸውን እንዲያደርጉ ቢፈቀድም አንድ ታሪክ እንዲሰሩ ግን ይገደዳሉ። ያው የውዴታ ግዴታ ማለት ነው። ይህም ከጨዋታው ባሻገር አሻራን የማሳረፍ ጉዳይ ሲሆን፤ በበዓሉ ማጠናቀቂያ ላይ ዛፎችና መድሃኒትነት ያላቸው እጽዋት መትከል ነው። ከዚያም አለፍ ብለው ቀደም ብለው የተተከሉ እጽዋትን የአካባቢን ስነ ምህዳር ለማስጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ያምናሉና እንክብካቤ ያደርጉላቸዋል። ይህ ደግሞ የሴቶችን እኩልነትና ነፃነትን ከማክበር ባለፈ ሴቶች በአካባቢያቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ንቁ ተሳታፊ እንደሆኑ ያረጋግጣልና ደስተኛ ሆነው ያደርጉታል።

ይህ የነጻነት ጊዜ ለሴቶች የውበትን ማሳያም ጊዜ ነው። በወቅቱ ሴቶች በፀጉር አሠራራቸው ከአልባሶ እስከ ግልብጭ፣ ከጋመ እስከ ድርብ፣ ጋሜ፣ ቁንጮ፣ ሳዱላና ቅርድድ ተሠርተው አደባባይ የሚውሉበት ነው። እንደ ሕንቆ፣ አልቦ፣ ድሪ፣ ድኮት፣ ጉትቻ፣ ማርዳ ፤ መስቀል በሚባሉ ጌታጌጦች ተውበው አለባበሳቸውም በመልጉም /ጥልፍ ቀሚስ/፣ ሹፎን፣ ጃርሲ ተውበው በልዕልና የሚታዩበት፣ በነፃነት ነግሠው የሚጫወቱበት ነው።

በአጠቃላይ እነዚህ የነጻነት ቀናት በማሳረጊያቸው ጭምር የተለያዩና ልዩ ትዝታን የሚጭሩ ዘላለም ለነጻነት ያለንን ትግል የሚጨምሩ ሆነው ዛሬ ድረስ ዘልቀዋል።

አሸንዳ/ሻደይ/አሸንድዬ/ሶለል እንግጫ ነቀላና አሸንዳና‹‹ዓይኒ ዋሪ›› ወዘተ እየተባለ የሚሰየመው በክረምት ወቅት ከሚበቅለው ተክል ጋር በማዛመድ የወጡ የመለምለም ምስጢራዊ ፍቺዎች በመሆናቸውም ለምድሪቱ ልምላሜ የሚሰጠው ክብርንም የሚያሳዩ መሆናቸውን ነጋሪ አያሻውም። እናም ይህንን ስም ያወጡለትን ቅጠል በወገባቸው ላይ አድርገው ፍስሃቸውን በየአደባባዩ እየሰበኩ ቀናትን የሚያሳልፉት ሴቶቹ፤ እስከ ነሐሴ 21 ድረስ በሚዘልቀው ቀናቸው ብዙ ሕግጋትንና እሴቶቻችንን የሚያስተምሩና ሰነድ ሆነው የሚቀርቡ እንደሆኑ ሁሉም ሰው መገንዘብ ይኖርበታል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ክረምት ተሻጋሪ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት

**አስናቀ ፀጋዬ**

በጎ ፍቃደኝነት በመንግስት አቅም መስራት የማይችሉና ህብረተሰቡ በግሉ ሊሰራቸው የማይችሉ ተግባራትን በጎ ፍቃደኞች ጥቅም ሳይፈልጉ ተሰባስበውና ተደራጅተው በጉልበታቸው፣ በእውቀታቸውና በገንዘባቸው የሚያከናውኑት ተግባር ነው:: በዚህ በጎ ተግባርም በአለም አቀፍ ደረጃ በርካታ እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎች በየአመቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ::

በኢትዮጵያም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አስተሳሰብ በህብረተሰቡ በተለይ ደግሞ በወጣቱ ዘንድ እየዳበረ በመምጣቱ፤ በመንግስትም በኩል አገልግሎቱ ተቋማዊ እንዲሆን በመደረጉ ለበርካቶች ተደራሽ ለመሆን በቅቷል:: በዚህም በርካታ እርዳታ የሚሹ ዜጎች ተጠቃሚ ለመሆን በቅተዋል:: በዚሁ አገልግሎት የሚሳተፉ በጎ ፍቀደኛ ወጣቶች ቁጥርም እያደገ መጥቷል::

ብዙ በተባለለት የዘንድሮው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በአስራ አንድ የተለያዩ ዘርፎች በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን፤ በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ ከ19 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች ተሳትፈዋል:: በሚከናወነው በዚሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም መንግስትና ህብረተሰቡ ሊያወጡ የሚችሉት 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ይድናል ተብሎ እንደሚጠበቅ መረጃዎች ጠቁመዋል:: አገልግሎቱም ከሰኔ 15 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ እንዲከናወን መርሃ ግብር ተይዞለታል::

በአዲስ አበባ ከተማም ወጣቶች በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ውስጥ በመሳተፍ በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ከፍተኛ ስራዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ::በዘንድሮ በጀት ዓመትም በከተማዋ ነዋሪዎች ዘንድ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ በተለያዩ ዘርፎች በተሰራው ሥራ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማዳን ተችሏል::

የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሁሌም በየአመቱ ክረምትን ጠብቆ የሚከናወን እንደሆነ ቢታወቅም የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ማህበር ‹‹በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ክረምት ተሻጋሪ ስራዎችን እያከናወንኩ ነው፤ ዘንድሮም አከናውናለሁ›› ይላል::

ወጣት ይሁነኝ መሀመድ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ማህበር ዋና ፀሃፊ ነው:: እርሱ እንደሚለው አጠቃላይ የበጎ ፍቃድ ተግባር በዋናነት የተጀመረው የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ከተመሰረተ ከሀያ አራት አመት በፊት ነበር:: በተደራጀ መልኩ ‹‹የክረምት›› በሚል የማህበሩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የተጀመረው ግን በ1995 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ወጣት ተማሪዎች በስራቸው ያሉ ወጣቶችን እንዲያስተምሩ በማድረግ ነው::

ከዛ በፊት በነበሩት ሁኔታዎች የኤች አይ ቪ ኤድስ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር የፔፕሲ ሱቆችን የማምጣት ስራዎች በማህበሩ በኩል ሲከናወኑ ቆይተዋል:: በኋላ ላይ የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት በጨመረበት ጊዜ የኤች አይ ኤድስ ታማሚዎችን የመንከባከብ፣ህክምና እንዲያገኙ የማድረግ፣ የማብላት፣ የማጠጣትና የመደገፍ ሲሰሩ ነበር:: ‹‹በኤች አይ ቪ ኤድስ ታማሚዎች ላይ የሚደርሰው ማግለልና መድልኦ ይቁም!›› የሚሉ እንቅስቃሴዎች ሲጀመሩም ማህበሩ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነበር::

ከዚሁ ጋር ተያይዞም ማህበሩ የኤች አይ ቪ ኤድስ ታማሚዎችን፣ ዝቀተኛ ገቢ ያላቸውንና የአቅመ ደካማ አረጋውያንን መኖሪያ ቤቶች የማደስ ስራዎችን በጊዜው በስፋት ሲሰራ ቆይቷል:: የችግኝ ተከላና እንክብካቤ እንዲሁም የፅዳት ስራም በወጣት ማህበሩ በኩል ሲካሄድ ነበር::

እንደ ዋና ወጣት ይሁነኝ ገለፃ በነዚህ ሂደቶች ሁሉ መንግስት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ ስራዎች ብቻ ሳይሆን የወጣቶችን ጉዳይ በአደረጃጀት ደረጃ የሚመለከት ተቋም አልነበረም:: በጊዜው የወጣቶች አደረጃጀት በወረዳ ደረጃ በማህበራዊ ዘርፍ ውስጥ ታቅፎ ነበር ሲሰራበት የቆየው እንጂ ራሱን የቻለና ወጣትን የሚመለከት ተቋም አልነበረም:: ከዚህም በኋላ ነው ወጣቶችን የሚመለከት ራሱን የቻለ ተቋም መቋቋም የጀመረው::

የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱ እንዳለ ሆኖ ወጣቶች የሚውሉባቸው ቦታዎች በሙሉ የሚታወቁ ባለመሆናቸው ማህበሩ ቀደም ብሎ ቦታዎች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተረክቦ የወጣቶች ማእከል ሊገነባ ይገባል በሚል በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቦታ አስፈቅዶ የወጣቶች ማእከል ገንብቶ እንደናሙና አሳይቶ በመላ ከተማዋ ሌሎች የወጣት ማእከላት እንዲገነቡ በር ከፍቷል::

ማህበሩ በበጋ የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ትራፊክ የማሳለጥ፣ አረጋውያንን የመንከባከብ፣ የቤት እድሳት፣ የኤች አይ ቪ ኤድስ ምርመራ፣ የስነ ተዋልዶ ጤና ትምህርት፣ ከአዲስ አበባና አጎራባች ክልሎች ጋር ያሉ ወጣቶችን በስራ የማገዝ ስራዎችን ያከናውናል:: በከተማዋ ደግሞ ‹‹በጎነት በሆስፒታል›› በሚል ከተማዋ የኢትዮጵያ ዋና መናገሻ እንደመሆኗ ከመላው ኢትዮጵያ ሪፈር ተፅፎላቸው ከተማዋ ውስጥ ባሉ የመንግስት ሆስፒታሎች ውስጥ ህክምናቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ ታካሚዎችን የመንከባከብ ስራም በማህበሩ በኩል ይከናወናል::

በተለይ ደግሞ ታማሚዎች ከሃኪሞች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት የቋንቋ ችግር ሲገጥማቸው በማስተርጎም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከባለፈው አመት ወዲህ በየካቲት አስራ ሁለትና አቤት ሆስፒታሎች ጀምሯል:: በዚህና በሌሎች መስኮች የማህበሩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እየሰፋ መጥቷል:: አገልግሎቱ ወደ ህብረተሰቡ ይበልጥ ተደራሽ እየሆነ መጥቷል:: ወጣቱም ከራሱ አልፎ ለሌሎች ማድረግን እየተለማመደ መጥቷል::

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር የወጣቶች የበጎ ፈቃድ ተግባርን መሰረት አድርጎ ከተቋቋመ 25 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ሁሉም ሰው በበጎ ፈቃድ ሥራ መሳተፍ አለብኝ ብሎ እንዲያስብ እና ባህል እንዲሆን የሚያስችሉ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል

ወጣት ይሁነኝ እንደሚናገረው የበጎ ፍቃድ አስተሳሰብ በመንግስት አቅም መሰራት የማይችሉና ህብረተሰቡ በግሉ ሊሰራቸው የማይችሉ ተግባራትን በጎ ፍቃደኞች ተሰባስበውና ተደራጅተው በጉልበታቸው፣ በዕውቀታቸው ከፍ ሲል ደግሞ ባላቸው አቅምና የሌሎችን አቅም ተጠቅመው የሚያከናውኑት ተግባር ነው:: ከዚህ አንፃር የማህበሩ ወጣቶች እነዚህን በጎ ስራዎች ሲያከናውኑ መንግስት ጥርጊያ መንገዱን ካመቻቸ ከመንግስት አቅም በላይ የሆኑ ስራዎችን ይሰራሉ::

በዘንድሮው የ2014 ዓ.ም የክረምት የወጣቶች በጎ ፍቃድ አገልግሎት የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ማህበር የተለያዩ የበጎ ፍቃድ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን ከያዘው ዕቅድ በላይ ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ሊያወጡ የሚችሉ ተግበራትን አከናውኗል:: ወጣቶች እስከ 50 ሺ የሚሆኑ በግማሽና ሙሉ ቀን እንዲሁም በሳምንት ውስጥ በሚደረጉ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ውስጥ እየተሳተፉ ይገኛሉ::

የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱ የበጀት አመቱ መዝጊያ ላይ የተጀመረ ቢሆንም ማህበሩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱን በበጋም ጭምር የሚያከናውን እንደመሆኑ በክረምት የሚሰራቸውን የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች እያከናወነ ወደ በጋው ይሻገራል::

በዚሁ የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የማህበሩ አባላት በተለያዩ አስራ ሶስት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዘርፎች እየተሳተፉ ይገኛሉ:: ከነዚህ ውስጥም በኪነ ጥበብ ዘርፍ ሙዚቃ፣ ቲያትርና የውዝዋዜ ዘርፎች ይገኙበታል:: በጎነት በሆስፒታል በሚለው ዘርፍም ቋንቋ በማስተርጎም፣ በህሙማን እንክብካቤ፣ ህሙማን በከተማዋ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ቦታዎችን በማሳየትና ከኮሮና ጋር የተያያዙ ስራዎችን የሚሰሩ ወጣቶች አሉ::

በተጨማሪም የሆስፒታሉን ዳታ ኢንኮድ የማድረግ፣ ፋይል የማደራጀትና በሌሎችም አምስት ዘርፎች ስራዎችን ያከናውናሉ:: በስፖርት ዘርፍም እንደዚሁ በእግር ኳስ፣ በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ቅዳሜና እሁድ ነዋሪውን ስፖርት በማሰራት ሰፋት ያለው የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን እያከናወኑ ይገኛሉ:: በፀጥታና ሰላም ጉዳዮች ላይም ወጣቶቹ በበጎ ፍቃድ ተሳታፊ ናቸው::

ከዚህ ባለፈ ወቅቱ ክረምት ነውና ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት የጎርፍ ተጋላጭነት መከላከል ስራዎችንም ወጣት ማህበሩ ሰርቷል:: የጎርፍ ጉዳት የደረሰባቸው የተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ላይም የቤት ማደስ ስራዎች ተከናውነዋል:: ወደፊትም የጎርፍ ቅድመ መከላከል ስራዎች በበጎ ፍቃድ የሚከናወኑ ይሆናል::

ወጣት ይሁነኝ እንደሚገልፀው፤ በአሁኑ ወቅት የበጎ ፍቃድ አስተሳሰብ በመንግስትም ጭምር ትልቅ ትኩረት እያገኘ የመጣና በአስተዳደር ደረጃም ለጉዳዩ እውቅና እያገኘ መጥቷል:: በገንዘብ መደገፍ፣ ጉልበት መስጠትና በእውቀት ማገዝ ባይቻል እንኳን በጎ ፍቃደኞች እያከናወኑት ያለው ተግባር ጠቃሚ ነው የሚለው አስተሳሰብ በስፋት ተደራሽ እየሆነ ይገኛል:: ይህም እንደጠንካራ ጎን የሚወሰድ ነው::

አንዳንድ ተቋማትም በጎ ፍቃደኝነትን በውል በመረዳት ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን በማቅረብ እገዛ እያደረጉ ይገኛሉ:: ከክልል ተፈናቅለው ለመጡ ዜጎችና የጎዳና ተዳዳሪዎች ለሚደረገው ምገባም በቀናነት የእውቀት፣ የገንዘብና ሌሎችንም ድጋፎች ያደርጋሉ:: ይህም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ግንዛቤው በይበልጥ እየሰፋ መምጣቱን ያሳያል::

የማህበሩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ስራ ክረምትን ተሻግሮ በበጋ ወቅትም የሚከናወን ነውና ወጣት በጎ ፍቃደኝነት በትምህርት ቤት፣ በአካባቢና በሰፈር ያለ በመሆኑ በቀጣይም በተለያዩ መልኩ የሚከናወን ይሆናል:: ከዚህ ባሻገር በመንግስት በኩል በበጎ ፍቃድ ሊሰሩ የሚችሉ ተግባራትን በውል ለይቶ በመደበኛነት ሌሎች ተግባራትን በአቅሙ ማከናወን ይጠበቅበታል::

ለአብነት ቤት ማደስ የወጣቶች የበጎ ፍቃድ ስራ ቢሆንም መንግስት ቤት ለሌላቸው ገንብቶ መስጠት አለበት:: ለዘላቂነት በጎ ፍቃደኝነቱ እንዳለ ሆኖ የተረጂነት አስተሳሰብ እንዳይጎለብት ጥረት መደረግ አለበት::መንግስት መሰረታዊ ነገሮችን ለዜጎች ሠርቶ በጎ ፍቃደኞች መንግስት መሸፈን ያልቻላቸውን ስራዎች ማከናወን ይጠበቅባቸዋል::

የማህበሩ ቀጣይ ትኩረትም በበጎ ፈቃድ ስራ የከተማዋንና እና የሀገሪቱን ሰላምና ጸጥታ ማስጠበቅ፣ የወጣቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እና የለማች ሀገር ለማድረግ በሚደረገው ሁለተናዊ ጥረት ወጣቱ ጉልህ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ነው::

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር የወጣቶች የበጎ ፈቃድ ተግባርን መሰረት አድርጎ ከተቋቋመ 25 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ሁሉም ሰው በበጎ ፈቃድ ሥራ መሳተፍ አለብኝ ብሎ እንዲያስብ እና ባህል እንዲሆን የሚያስችሉ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል::

ሀገር ተረካቢ ወጣቶችን ከማፍራት አኳያም ማህበሩ በክረምት ወራት በቤታቸው የሚገኙ በርካታ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአልባሌ ቦታ እንዳያሳልፉ ከማድረግ በተጨማሪ በገንዘብ የማይተመን የማጠናከሪያ ትምህርት የመስጠት ስራም ሰርቷል::

# የምድር በረከት

## ከማእድን ዘርፉ የሚጠበቀውን ተጠቃሚነት የማሳደግ ቁርጠኝነት - በኦሮሚያ ክልል

**ስምስም መንግሥቱ**

*መንግሥት በአስር አመቱ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው መሪ እቅዱ ላይ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ላቅ ያለ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ብሎ ከለያቸውና በትኩረት እየሰራባቸው ከሚገኙ ጥቂት የኢኮኖሚ አምዶች አንዱ የማዕድን ዘርፍ ነው::*

ይህን የማዕድን ዘርፍ በተደራጀ መልኩ አልምቶ ሀገራዊ እቅዱን ማሳካት ከሚጠበቅባቸው መካከል ክልሎች ይጠቀሳሉ:: ይህን መነሻ በማድረግ በኦሮሚያ ክልል ስለሚገኙ የማዕድን አይነቶች፣ የማዕድን ሀብቶቹን በተደራጀ መልኩ አልምቶ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ እየተደረገ ስላለው ጥረትና ስለተገኙ ለውጦች ከኦሮሚያ ማዕድን ልማት ባለሥልጣን ኃላፊ ከአቶ ተስፋዬ መገርሣ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበናል::

**አዲስዘመን፡- የክልሉን የማዕድን ሀብቶች በየዘርፋቸው ለይቶና አደራጅቶ ለማልማት ምን እየተሰራ ነው? ዋና ዋና የሚባሉ የማዕድን ሀብቶችን ቢገልጹልን::**

**አቶ ተስፋዬ፤** በክልሉ ሰፊ የማዕድን ሀብት አለ፤ በጥናት በተደገፈ ሁኔታ መጠኑንም ሆነ የማዕድን አይነቶቹ በየትኛው የክልሉ አካባቢ እንደሚገኙ መግለጽ አለመቻሉ ግን አንድ ክፍተት ነው:: ይህም የቀድሞው መንግሥት ለዘርፉ ከሰጠው ትኩረት አናሳነት ጋር ይያያዛል:: በወቅቱ የማዕድን ሥራው የሚከናወነው በወሰኑ ባለሀብቶች ነው:: ለዘርፉ የሚመደበው በጀትም አነስተኛ ነበር:: የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የሚባለው ተቋም ካልሆነ፣ በዘርፉ ላይ አተኩረው ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ተቋማት ነበሩ ማለትም አይቻልም::

**አዲስ ዘመን፤ በክልሉ በጥናት የተደገፈ የማዕድን ሀብት መኖሩ ካልተረጋገጠ ሀብቱ ስለመኖሩ እንዴት እርግጠኛ መሆን ይቻላል? ክፍተቶቹ አሁንም ቀጥለዋል ማለት ነው?**

**አቶ ተስፋዬ፤** የቀድሞውን አሰራርና በአሰራር ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት ያስቀደምኩት ከሀገራዊ ለውጡ በኃላ ያለውን እንቅስቃሴ በንጽጽር ለማሳየት ነው:: ከአራት አመታት ወዲህ በተደረገው እንቅስቃሴ በኦሮሚያ ክልል የተቋም አደረጃጀት ለውጥ ተደርጓል:: የማዕድን ዘርፉ በክልሉ በባለስልጣን ደረጃ ራሱን ችሎ ተቋቁሟል:: የተቋመውም ሶስት ዓላማዎችን መሠረት ባደረገ መልኩ ነው:: አንዱ አላማም ክልል ውስጥ የሚገኘውን የማዕድን ሀብት ተደራሽ የማድረግ፣ ቆጠራዎችን ማካሄድ፣ በጥልቀት የመለየትና ማጥናት ነው:: በዚሁ መሠረትም ማዕድኖቹን በአይነትና በመጠን መለየት ተችሏል::

ሁለተኛው ዓላማ በጥናት የተለዩት ሀብቶች እንዴት ጥቅም ላይ ይዋሉ የሚል ነው:: ሶስተኛው ደግሞ የማዕድን ልማቱ በተፈጥሮና በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ ማድረግ ነው:: በዚህ መልኩ ባለፉት ሶስት አመታት ሲሰራ ቆይቷል::

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ እንዳሉት ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አናሳ ስለነበር ውጤቱም አጥጋቢ አልሆነም:: ከሀገራዊ ለውጡ በፊትም ዘርፉን የሚመሩ በየክልሉ አደረጃጀቶች ነበሩ:: ችግሩ የአሰራር ሥርአት አለመዘርጋቱ ነው? ወይንስ ዘርፉ ከቢሮ ደረጃ ከፍ ብሎ አለመመራቱ ወይንም አለመደራጀቱ ላይ ነው?**

**አቶተስፋዬ፡-** አንደኛ በክልሉ ራሱን ችሎ የተደራጀ ቢሮ አልነበረም:: ወጥ የሆነ አደረጃጀትም አልነበረም:: አንዴ በቢሮ ደረጃ ይዋቀራል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከሌሎች ተቋማት ጋር በጥምረት አንድ ክፍል ሆኖ እንዲሰራ ይደረጋል::

በክልል ደረጃም የማዕድን ሥራዎች አዋጅ አልነበረም:: ለመጀመሪያ ጊዜ የኦሮሚያ የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ጨፌ ኦሮሚያ ላይ ቀርቦ የፀደቀው በ2011ዓም ከሀገራዊ ለውጥ በኃላ ነው:: የክልሉ የማዕድን ሀብት በፌዴራል ደረጃ ሲወጡ በነበሩ አዋጆች ነው ሲመራ የቆየው::

አንዱ ችግር ተቋማዊ አደረጃጀት ነው:: ሌላው በክልል ደረጃ ፖሊሲና አዋጅ አለመኖር ነው:: ሶስተኛው ደግሞ እስከታችኛው እርከን የተዘረጋ መዋቅር አለመኖር ነው::በአጠቃላይ ከላይ እስከታች የተደራጀ ነገር አልነበረም:: ብዙ ሥራዎች ቢቀሩም አሁን እነዚህ ነገሮች በመቀረፍ ላይ ናቸው::

**አዲስዘመን፡- የአደረጃጀት ክፍተቶቹን ለመቅረፍ** ጥረት ከተደረገ ወዲህ ስለተከናወኑት ተግባራት ቢገልጹልን?

**አቶ ተስፋዬ፡-** የተቋም አደረጃጀቱ ከተፈጠረ በኃላ ክልሉ ውስጥ ያሉትን የማዕድን አይነቶች የመለየት ሥራ ተከናውኗል:: ለዚህ ሥራም አስፈላጊውን በጀት በመመደብና በማዕድን ዘርፍ ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ባለሙያዎችን በማሳተፍ ሀብቱን ለመለየት ተሰርቷል::

በዚህም ወደ 48 የሚደርሱ የማዕድን አይነቶች ማግኘት ተችሏል:: ከዚህ በኃላ ለመጀመሪያ ጊዜም በኦሮሚያ ውስጥ በጥናት ታግዞ በተከናወነ የመለየት ሥራ የተገኘውን የማዕድን አይነት ለማስተዋወቅ ኤግዚቢሽን ተካሂዷል::

ባለስልጣኑ እነዚህን በጥናት የተደገፉ ሥራዎች ለማከናወን ወደ ሥራ ሲገባ ኤክስፖሎሬሽን የሚባል ወይንም ማዕድናቱ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ክፍል አዋቅሯል:: በዚህ ክፍል በተከናወነ ሥራም አዳዲስ ማዕድናትን ማግኘት ተችሏል::

እስካሁን ባለው ሥራም በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ማዕድናት መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተሰራ እንጂ በመጠንና በአይነት ዝርዝር ሥራዎች በቀጣይ ይከናወናሉ:: ባለስልጣኑም ገና በአዲስ የተዋቀረ በመሆኑ ጠለቅ ያለ ተግባር ውስጥ አልገባም:: ጥልቅ በሆነው ሥራ ላይ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና ባለሀብቶች እንዲሳተፉ የማመቻቸቱ ሥራ ቀጣይ ተግባር ይሆናል:: በቀላሉ ሊለሙ በሚችሉት ደግሞ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርባቸው ጎን ለጎን ይሰራል::

**አዲስ ዘመን፡- ከ48ቱ የማዕድን አይነቶች ዋና ዋና የሚባሉትን ቢጠቅሱልን?**

**አቶ ተስፋዬ፡** ዋና ዋና ማእድናቱ ወርቅ፣ ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውሉ ኒኬል፣ ክሮማይት እንዲሁም እንደ ኤመራልድ፣ ሳፋየር፣ ሩቢ፣ ታንታለም የመሳሰሉ የጌጣጌጥ ማዕድናት ናቸው:: አብዛኞቹ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙም ናቸው:: ከማዕድናቱ መካከል ኢትዮጵያን ከዓለም አስረኛ ደረጃ ላይ ሊያስጠቅሳት የሚችለው ታንታለም የተባለው አንዱ ነው፤ ይህ ማእድን በጣም አብረቅራቂና ውብ ነው::

ማዕድኑ በኤሌክትሪክ ኃይል ለሚሞሉ ተሽከርካሪዎችና ለተንቀሳቃሽ ስልክ ባትሪ ግብአት የሚውል መሆኑ ተረጋግጧል:: ማዕድኑ በክልሉ ጉጂ ዞን ሰባቦር በሚባል ወረዳ በስፋት መኖሩ ታውቋል:: ማዕድኑ ፊትም ይመረት እንደነበር መረጃዎች ቢኖሩም፣ አሁን ላይ ጥሬውን ለገበያ ከማቅረብ ይልቅ እሴት ጨምሮ እንዲቀርብ በማድረግ የበለጠ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ እየተሰራ ነው::

አዲስ ዘመን፡ እነዚህ ዋና ዋና የማዕድን አይነቶች በክልሉ በየትኞቹ አካባቢዎች እንደሚገኙ ተለይቷል?

አቶ ተስፋዬ፡- በሁለቱ የጉጂ ዞኖች፣ ቦረና እና ሶስቱ የወለጋ ዞኖች እንዲሁም ኢሊባቦር ወርቅ፣ ብረትና ብረት ነክ የሆኑ ማዕድናት ይገኙባቸዋል:: ማዕከላዊ ወይንም ሸዋ ዞኖች ላይ ደግሞ ለኢንዱስትሪና ለግንባታ ግብአት ሊውሉ የሚችሉ፣ ጅማ አካባቢ ደግሞ የድንጋይ ከሰል የሚገኙባቸው ናቸው:: እነዚህ በዋናነት ተጠቀሱ እንጂ በክልሉ 21 ዞኖችም የተለያዩ የማዕድን አይነቶች ይገኛሉ::

**አዲስ ዘመን፡- የማዕድን ዘርፉን ክልልን አካባቢንና ሀገርን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ክልሉ ያለው ቁርጠኝነት እንዴት ይገለጻል ?**

**አቶ ተስፋዬ፡-** አንዱ ትኩረት የማግኘት ጉዳይ ነው:: ትኩረት ከተገኘ በኃላ ደግሞ ዘርፉን ወደላቀ ተጠቃሚነት ማሸጋገር ነው:: ይህን ለማድረግ በእውቀት ላይ ተመስርቶ መሥራት ይጠበቃል:: እንደ ሀገር ያሉብን ክፍተት አንዱ የአቅም ውስንነት ነው:: ሌላው የእውቀት ማነስ ነው:: እነዚህን ውስንነቶች ለመቅረፍ እየተሰራ ነው:: የዘርፉ ሥነምግባር የሚጠይቀውን አሟልቶ ለመንቀሳቀስ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር እየተሰራ ሲሆን፣ዩኒቨርስቲዎቹ የልህቀት ማዕከል እንዲኖራቸው በተለይም በጂኦሳይንስ የምርምር ማዕከል ላይ ትኩረት አድርገው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ:: ባለስልጣኑም አብሮ እየሰራ ነው::

በዚህ ረገድ በመስራት በኩል በተለይም ከወለጋ ዩኒቨርስቲ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመናል:: ጉጂ ውስጥ ከሚገኘው ቡሌሆራ ዩኒቨርስቲ ጋርም ለመፈራረም ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው::

ማዕድን ላይ ስንሰራ ፖሊሲ፣ህግና መዋቅሮች ላይም ፍተሻ በማድረግ መስተካከል ያለባቸውን ለማስተካከል ጥረት አድርገናል:: ለሚቀጥሉት አስር አመታት ዘርፉ በምን ሁኔታ መመራት እንዳለበት ፍኖተ ካርታ (ሮድማፕ) ተዘጋጅቷል:: በፍኖተ ካርታው ላይም አምስት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተው ተቀምጠዋል::

የመጀመሪያው ተግባር የሀብት ልየታ ሥራ ሲሆን፣ የክልሉን ሀብት በካርታ ማመላከት (ሪሶርስ ማፕ መሥራት) ነው:: የሚገኘውን የሀብት አይነትና መጠን የሚያሳይ ሥራ መሰራት እንዳለበት ነው አቅጣጫ የተቀመጠው::

እንደ ማዕድኑ ባህሪ ተለይቶ እንዴት ጥቅም ላይ ይዋል የሚለው ደግሞ ሌላው አቅጣጫ ነው:: ይህ ከቴክኖሎጂ ጋር ይያያዛል:: በግዥ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለመተካት ምን አይነት ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚገባ የሚያመላክት አሰራር ነው::

ሶስተኛው ተግባር ሀብቱ በሚገኝባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተጠቃሚነት ጉዳይ ነው:: ይህ ጉዳይ ህብረተሰቡም የሚያነሳው በመሆኑ ምላሽ ማግኘት አለበት:: የኢንቨስትመንት ተሳትፎም በተመሳሳይ ይነሳል:: ተጠቃሚነት፣ኢንቨስትመንትና የአካባቢ ደህንነት ጉዳዮች ከማዕድን ልማቱ ጋር እንዴት ተጣጥመው መከናወን አለባቸው የሚለው ትኩረት ተሰጥቶታል::

ሶስተኛው የትኩረት አቅጣጫ ፍቃድ አሰጣጥ፣ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚሉትን ይመለከታል:: የማዕድን ዘርፉ የግለሰቦችን ኪስ ብቻ ከሚያደልብ ይልቅ የሀገር ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ እንዴት መሥራት አለብን ብለን እየሰራን ነው:: ፍቃድ መስጠት ብቻ ሳይሆን የዚህ ባለስልጣን ድርሻ የሰጠውን ፍቃድ በአግባቡ የማስተዳደር ግዴታም ስላለበት በዚህ ታሳቢነት ጠንክረን እየሰራን እንገኛለን::

የማዕድን ዘርፉ በአካባቢ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርስ የሚችለውን ተጽእኖ ለመቀነስ መሰራት አለበት:: ይህም አራተኛው የትኩረት አቅጣጫ ነው:: ልማቱ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ለማዕድን ፍለጋ የሚካሄድ ቁፋሮ ካለቀ በኃላ ጉድጓድ ክፍት የሚተውበት ሁኔታ ይታያል:: ይህን መሰሉ ተግባር መታረም ይኖርበታል::

ህብረተሰቡ አብሮ የሚለማበት ሁኔታ መፈጠር አለበት:: መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቷል:: ሥራዎች መሰራት ያለባቸው መንግሥት የሰጠውን ትኩረት ሊመጥን በሚችል ተቋም ነው፤ ይህን መገንባት መቻል አለብን በሚል በትኩረት እየተሰራ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ማዕድኑን በቁፋሮ ከመሬት ውስጥ የሚያወጡት የድካማቸውን ዋጋ እንደማያገኙና ትኩረትም እንዳልተሰጣቸው ቅሬታ ያቀርባሉ:: በዚህ ሳይስ ምን ይላሉ?**

**አቶ ተስፋዬ፡-** ዘርፉ የሥራ ዕድሎች የሚፈጠሩበት ማድረግም ሌላው የቤት ሥራችን ብቻ ሳይሆን ግብችንም ነው:: በቀላሉ ሊለሙ የሚችሉ ማዕድናት ላይ ማህበረሰቡን ማዕከል ባደረገ መልኩ ልማቱ እንዲከናወን ታቅዷል:: ለእዚህም የደለል ወርቅ ማምረት በአብነት ይጠቀሳል:: ህብረተሰቡ እነዚህን ማእድናት በቀላሉ ሊያለማቸው ይችላል፤ መጠነኛ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀም ለማድረግ ግን ይሰራል::

ካፒታል በሚጠይቁ ልማቶች ላይም ቢሆን ማእድኑ ያለበት አካባቢ ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ተመቻችቷል:: ይህም በድንጋይ ከሰል ልማት ላይ በተግባር ተከናውኗል:: ይህ የሚደረገው አንድም ህብረተሰቡ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ለማድረግ ነው::

ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ማዕድን የሚያዘዋውሩ ግለሰቦች ላይ ባለስልጣኑ እርምጃ እየወሰደ ይገኛል::



**የኦሮሚያ ክልል ማዕድን ልማት ባለሥልጣን ኃላፊ አቶ ተስፋዬ መገርሣ፤**

በቅርቡም ባደረገው የክትትልና ቁጥጥር ስራ የውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር የተሳተፉበት ህገወጥ ተግባር ተደርሶበት 22 ህገወጦችን ተይዘው ለህግ ቀርበዋል::

አዲስ ዘመን፡- በቴክኖሎጂ በመደገፍ ለውጥ ለማምጣት ጥረት ይደረጋል ሲባል ምን ማለት ነው?

አቶ ተስፋዬ፡- ዓለም የሚጠቀምበትን ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ነው ጥረቱ:: ለአብነትም በባህላዊ መንገድ ወርቅ የሚያመርቱ ጉልበታቸውን ከማባከናቸው በተጨማሪ በቁፋሮ ያወጡትን ማዕድን በአግባቡ እያጣሩ አይደለም::

ከአንድ ኪሎ አፈር ውስጥ መቶ በመቶ ማዕድኑን ማውጣት እየተጠበቀባቸው አነስተኛ መጠን ያለው ወርቅ ነው የሚያወጡት:: ይሄ ብክነት ነው:: ወርቁን ከአፈር ውስጥ የሚያጣራ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ችግሩን ማስቀረት የሚቻልበትን መንገድ ለማመቻቸት ይሰራል::

ቴክኖሎጂውን መንግሥትም የግሉም ዘርፍም ለወርቅ አምራች ማህበራት ማቅረብ ይችላሉ:: አቅርቦቱንም ፕሮጀክት ቀርጾ መተግበር ይቻላል:: ዓለምአቀፍ ድርጅቶችም ሊተባበሩ ይችላሉ:: በአሁኑ ጊዜም አንድ የካናዳ ድርጅት ወደ ስምንት የወርቅ ማጠቢያ ማሽኖች አቅርቦልናል:: አምራቾቹ ስልጠና ወስደው መጠቀም ከጀመሩና ጥቅሙንም ከተገነዘቡ በኃላ በራሳቸው ለመግዛት ይነሳሳሉ::

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ በ2014 በጀት አመት በማዕድን ልማት በኢኮኖሚ ላይ ስላበረከተው አስተዋጽኦና የ2015 በጀት አመት እቅድ ቢገልጹልን?**

**አቶ ተስፋዬ፡-** በወርቅ ማዕድን ብቻ ወደ 4ሺ680 ኪሎግራም ወርቅ ወደ ብሄራዊ ባንክ እንዲገባ ተደርጓል:: ከዚህ ውስጥ 50 በመቶው በማህበራት ነው የተመረተው:: ከዚህም ወደ 314 /ሶስት መቶ አስራአራት / ሚሊየን ዶላር ገቢ ተገኝቷል:: ወደ 461ሺቶን የድንጋይ ከሰል ለፋብሪካዎች ቀርቧል::

በዘርፉ ለ156ሺ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በእቅድ ተይዞ ከዚህ ውስጥ ለ126ሺ ዜጎች ሥራ ተፈጥሯል:: በአጠቃላይ በዘርፉ በወጭ ንግዱም ሆነ በሀገር ውስጥ ግብአትን ለመተካት በተደረገው እንቅስቃሴ ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል::

ዘርፉ ኢኮኖሚውን ከፍ በማድረግ ረገድ ድርሻው ትልቅ እንደሆነ ማሳየት ተጀምሯል:: በቀጣይ እቅድ መልካም አፈጻፀሙን ማስቀጠል ክፍተቶችን ደግሞ በማረም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ይሰራል:: በተለይም እሴት የተጨመረበት ሥራ በመሥራት የውጭ ንግዱን ማሳደግ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ላይ በትኩረት ይሰራል:: የሥራ ዕድል መፍጠር ላይም እንዲሁ ይሰራል::

**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ መጠይቁ ላደረጉልኝ ትብብር አመሰግናለሁ::**

**አቶ ተስፋዬ፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ድርና ማግ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

‹ትሁት..አንቺ ትሁት..› በእንቅልፍ ልቤ የእናቴን ድምጽ ሰማሁት:: እናቴ በእውኔ ብቻ አይደለም በህልሜም ያለች ሴት ነች:: በህይወቴ የትም ቦታ አለች:: በሴትነቴ ጉራንጉር፣ በሰውነቴ እንጦሮጦስ ውስጥ የትም አገኛታለው:: ብዳብሳት የትም የማላጣት ሴት ናት:: ከእማዬ በቀር ተኝቼ የማልመው ህልም የለኝም:: የቀን ታሪኮቻችንን እያለምኩ ነው ከእንቅልፌ የምነቃው.. የምነቃውም እንዲህ እንደዛሬው በጥሪዋ ነው:: በህልሜ የማይመጣ ፊት፣ የማላየው ገጽ የላትም:: ቤታችን ካለችው መደብ ላይ ቁጭ ብላ እየፈተለች አሊያም እንዝርቷን እያሾረች ህልሜ ይጀምራል:: የህልሜ መቋጫ ጥሪዋ ነው:: ከእውኔም በህልሜም ሴትነቴ ውስጥ ተሰንቅራ የትም አያታለው::

በእናቴ ጥሪ ከእንቅልፌ ተቀሰቀስኩ:: ህልሜን ሳልጨርስ አልሜያት ሳላበቃ:: አልነጋም እኮ አባዬ ለገና የገዛው ከመታረድ የተረፈው የቤታችን አውራ ዶሮ ከጮኸ አልቆየም:: ለምን በዚህ ለሊት ተነስታ እንደምታስነሳኝ ሊገባኝ አልቻለም:: ጥሪዋ ቢሰማኝም እንቅልፌን ስላልጨረስኩ አቤት ማለት አልቻልኩም:: እንቅልፍ ጨርሶ ጠዋት መነሳት ምን እንደሚመስል አላውቅም:: እንደ መርዶ ነጋሪ ለማኝ ሳይፀዳዳ በውርጩ ነቅቼ የቤታችንን እዳሪ ነፍስ የምዘራበት እኔ ነኝ::

‹እስከ አሁን ተዘፍዝፈሽ..ቀኑን ሙሉ ተኝተሽ ልትውይ ነው እንዴ?..በይ ተነሽ› ብላ ጆሮ ግንዴ ላይ አንባረቀችብኝ:: እንቅልፌ ብቻ አይደለም ቀልቤም ትቶኝ ሄደ:: እናቴ የቤታችን ሰይጣን ናት:: አባቴ ደግሞ የቤታችን መላዕክ:: በነዘሲህ ሁለት መንፈሶች የምሰቃየው ደግሞ እኔ ነኝ:: ታላቅ ወንድሜ አግብቶ ከእናቴ ሰይጣንነት ተገላግሏል:: እኔም መች ይሆን ከዚህ ቤት ወጥቼ ከእናቴ ሰይጣንነት የምገላገለው ስል አስባለው:: አግብቶ የሚወስደኝ፣ ከእናቴ የሚገላግለኝ አንድ ወንድ ማጣቴ ይቆጨኛል:: የሴት ልጅ ተስፋዋ ወንድ መሆኑን ሳስብ እናደዳለው:: ሴት ልጅ ከእናት አባቷ ቤት ለመውጣት ከማግባት ውጪ ምንም አማራጭ እንደሌላት ሳስብ ሴት መሆንን እኮንናለው:: ወንድ ብሆን የእናቴ ሰይጣንነት ባልተሰማኝ ነበር እላለው:: ከእናቴ ሰይጣንነት ለመገላገል ስል ወንድነትን እናፍቃለው:: አጠገቤ እንደ መላዕክ በዝምታ የሚኖር አባት ስላለኝ የእናቴ ሰይጣንነት ጠልቆ አይሰማኝም::

እናቴ የኔን መተኛት ቀኑን ሙሉ አለችው:: እናቴ ቀንና ሰዐት እንዴት እንደምትቆጥር አላውቅም:: ገና እኮ ከለሊቱ አስራ አንድ ሰዐት ነው:: ገና እኮ አውራ ዶሯችን መጮህ አላቆመም:: ይሄን ከእኩለ ቀን ያመለጠ ለሊት ቀን ሙሉ አለችው..እስካሁን ተዘፍዝፈሽ አለችኝ:: ተነሳሁ.. ከዚህ በፊት እንደነቃሁባቸው ማዕልቶች እየተነጫነጭኩ.. እያጉረመረምኩ:: ከአባቴ ዝምታን ከእናቴ ጉርምርምታን ወርሻለው:: በሰይጣንና በመላዕክት መሀል መኖር ምን እንደሚመስል እኔ ናሙና ነኝ::

ገና እኮ የለሊት ልብሴን አልቀየርኩም..ገና እኮ ደጅ አልወጣሁም..ገና እኮ ፊቴን አላጸዳሁም ‹ዛሬ የአመቱ ገብርኤል ነው፣ አዲሱን ነጠላዬን አውጪልኝ ቤተክሲያን ስሜ ልምጣ› አለችኝ:: ጉስቁልናዬ ጀመረ:: ባደፈ ፊትና ገላ ከነለሀጩ የእናቴን አዲስ ነጠላ ፍለጋ ጀመርኩ:: ከግማሽ ሰዐት ፍለጋ በኋላ አዲሱ ነጠላዋ ተገኘ:: እናቴ እቃ ስታስቀምጥ በግራ እጇ ነው መሰለኝ ቶሎ አይገኝም:: እናቴ አስቀምጣው ቶሎ የምታገኘው እንዝርትና ጥጧን ነው:: ከምትቀመጥበት መደብ ውጪ የትም ስለማታስቀምጠው በቀላሉ ታገኘዋለች::

አዲሱን ነጠላዋን አቀበልኳት:: ‹ስመለስ የምጠጣው ቆንጆ ቡና አፍልተሽ እንድትጠብቂኝ› ከምትል ቀጭን ትዕዛዝ ጋር ነጠላዋን ተቀበለችኝ::

‹ቆንጆ ቡና እንዴት ነው? አልኳት::

‹ቆንጆ ቡና ሳታውቂ ነው ሴት የሆንሽው? አለችኝ::

ጥሎብኝ ሙያ የለኝም..ሙያ የለሽ መሆኔን ደግሞ ከአባቴ በቀር ድፍን ሰፈራችን ያውቀዋል:: እናቴ ‹ምን ይሆን የሚጣፈጥልሽ? ብላኝ ታውቃለች:: አባቴ ግን ለምን እንደሆነ አላውቅም እኔ ካላፈላሁለት ቡና አይጠጣም:: እኔ ምግብ ካልሰራሁለት አይበላም ለምን ስለው ያንቺ ሁሉ ነገር ያስደስተኛል ይለኛል:: አባቴ መላዕክ ካልሆነ ምን ሊባል ይችላል? እማዬ የምታዘኝን ከአባቴ ጋር ለሁለት ሰርተን እናውቃለን:: አይደለም ሊያዘኝ..አይደለም በሌሊት ሊቀሰቅሰኝ ቀርቶ በእማዬ ትዕዛዝ ውስጥ አብሮኝ የሚለፋ አጋሬ ነው::

‹ስሚ አንቺ ረኸጥ..›አለችኝ እናቴ::

ልሰማት ቀና አልኩኝ..

‹ቆንጆ ቡና ማለት ያልወፈረ፣ ያልቀጠነ ያልመረረ ቡና ነው:: ስመጣ አሁን ያልኩሽን ቡና አፍልተሽ እንድትጠብቂኝ› ስትል ነጠላዋን እያጣፋች ገላመጠችኝ:: ከአጠገቧ ስሄድ ‹ይብላኝ ሴት ናት ብሎ ለሚያገባሽ› ስትለኝ ሰማኋት::

ምን ረስታ እንደሆነ እንጃ ደግሞ ወደ ሳሎን ተመለሰች:: እናቴ መንቆራጠጥ ልማዳ ነው..ያንቆራጥጣታል:: ከሄደችበት ተመልሳ ‹ምናለ ዛሬ እንኳን ቤተክርስቲያን ብትሄድ? አለችው አባቴን::

አባቴ ዝም አላት..ከየት እንዳመጣው እንጃ ለእናቴ የሚሆን ብዙ ዝምታ አለው::

‹በመቁረቢያ እድሜህ እዚህ ተጋድመህ..አንተን ብሎ ወንድ› ስትለው ሰማሁ:: በአባቴ እንደዛ መባል ስቅጥጥ አለኝ:: እናቴ አባቴን አታከብረውም:: የሴት ልጅ ውበቷ ምኗ ነው ላለኝ የምመልሰው ብዙ መልስ አለኝ:: ከእናቴ ነውረኛ ሴትነት ውስጥ የቀሰምኩት:: አባቴ አሳዘነኝ..ቀና ብዬ ሳየው በወትሮ ዝምታው ውስጥ ነው:: በዝምታው ውስጥ ምን እንደሚያስብ ባውቅ እላለው::

ከአባቴ ወደ እኔ ዞራ..‹እንደ ነገርኩሽ ስመጣ መራራ ቡና እንዳታጨኝ፣ አንቺ እንደሆነ ልብ የለሽም› ብላኝ ወጥታ ሄደች:: እናቴ ሳርፍ አትወድም..የሆነ ነገር ፈጥራ የሆነ ነገር ትለኛለች እንጂ እሷ እየፈተለች እኔ እያወራኋት አጠገቧ እንድቀመጥ አትፈልግም:: የምትፈትለውን ጥጥ አጠገቧ ሆኜ ስፈለቅቅላት እንኳን ያገዝኳት አይመስላትም:: ‹እዚህ ከምትዘረፈጪ እስኪ ሂጂና ለእግሬ ውሀ አሙቂልኝ ትለኛለች:: ውሀውን አሙቄ እግሯን አጥቤያት አጠገቧ ቁጭ ስል:: እንግዲህ መጣሽ በወሬ ልታደርቂኝ..ሂጂና ትላንት የዘፈዘፍኩትን ልብስ አጥበሽ ስቀይ ትለኛለች:: የተዘፈዘፈውን ልብስ አጥቤ ሰቅዬ ቤት ስገባ ‹ከእትዬ ተዋበች ቤት ነገ የሚመለስ አንድ ስኒ ቡና ተበድረሽ ነይ ትለኝና ወደዛ እሄዳለው፡: እናቴ አጠገብ ሆኜ እናቴ ትናፍቀኛለች:: እንደ ልጅ አጠገቧ ቁጭ ብዬ የሆዴን ያወራኋት ግዜ የለም:: ለነገሩ እሷም አርፋ አታውቅም..ስትፈትልና ስትደውር ሸማኔ ቤት ስትመላለስ ነው የምትውለው:: ሰፈሩ ውስጥ ፈትላ ጋቢ ያላለበሰችው አንድም የለም:: የዛሬ አመት የተዳረው ታላቅ ወንድሜ እንኳን በእናቴ ጋቢ የተዳረ ነው:: እኔ ብቻ ነኝ ውጤት ሳይመጣልኝ ቤት የእናቴ ተላላኪ ሆኜ የተቀመጥኩት:: ዩኒቨርሲቲ የሚማረው ታናሽ ወንድሜ በእናቴ ጋቢ ላለመመረቅ ከአሁኑ ማስጠንቀቂያ እየላከልን ነው::

አባቴ በዝምታ የሚያምን ዝምታ ነው:: ከእናቴ ጫጫታ ይልቅ የአባቴ ዝምታ በእግዜር ፊት የሚሰማ ይመስለኛል:: ዛሬ ከነጋ እንኳን እኔንና ተከራዮቹን ስንት ግዜ በማይሆን ነገር ተቆጣችን:: እንግዲህ ይቺ ናት እናቴ..በዚህ ልብና ነፍሷ ነው ለተማጽኖ እግዜር ቤት የምትሄደው::

እንደ ምትፈለቅቀው ጥጥ፣ እንደ ምታሾረው እንዝርት እጇ ላይ ነኝ:: እንደ ቋጨችው ሸማ፣ እንደ ፈተለችው ድርና ማግ ከታሪኳ አልጠፋም..ከታሪኬ አጠፋም:: እኔና እናቴ የአንድ ሳንቲም ሁለት መልኮች ነን..ዘውድና ጎፈር:: የጥፍሬ ጥፍረ መጥምጥ ናት..የመዳፌም አይበሉባ:: የመረቧ አሳ ነኝ..የጣቶቿም ጓንት::

# ዓለም አቀፍ

## በካቡል የመስጊድ ጥቃት በርካቶች ሞቱ



ሼክ ረሒሙላሕ ሐቀኒ

በአፍጋኒስታን ዋና ከተማ ካቡል በደረሰ አንድ የመስጊድ ውስጥ የቦምብ ጥቃት በርካታ ሰዎች ሞቱ።በምሽት ሰዓት ይደረግ በነበረ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ነው ቦምቡ የፈነዳው።እስከአሁን በጥቃቱ ሦስት ሰዎች ሲሞቱ በርካቶች ቆስለዋል።የታሊባን ፖሊስ ቃል አቀባይ ካሊድ ዛድራን በሰሜን ምዕራብ ካቡል ሌላ ፍንዳታ እንደተሰማ ለአገሬው ሚዲያ ተናግረዋል።

ዘገባዎች እንደሚያሳዩት ከሆነ በዚህ የትናንቱ ፍንዳታ የሲዲቂ መስጊድ ኢማምን ጨምሮ የበርካቶች ሕይወት አልፏል።እስከአሁን ጥቃቱ በማን እንደተፈጸመ የታወቀ ነገር የለም።አንድ የታሊባን አስተዳደርን በመደገፍ የሚታወቁ መንፈሳዊ መሪ በቅርብ ሳምንታት ውስጥ በሌላ ፍንዳታ መገደላቸው የሚታወስ ነው።ለዚያ ጥቃት አይ ኤስ ኃላፊነቱን ወስዶ ነበር።

አንድ በካቡል ቅርንጫፍ ቢሮ ያለው የጣሊያን የረድኤት ድርጅት በትናንቱ ጥቃት ሦስት ሰዎች ስለመሞታቸውና 27 ሰዎች ክፉኛ ስለመቁሰላቸው ማረጋገጫ ሰጥቷል።ከቆሰሉት መካከል የሰባት ዓመት አዳጊን ጨምሮ በርካታ ሕጻናት ይገኙበታል።አንድ የታሊባን የደኅንነት ባለሥልጣን ለሮይተርስ እንደተናገሩት ደግሞ በድምሩ 35 ሰዎች ተገድለዋል፣ በርካቶች ቆስለዋል። እንደ እርሳቸው ከሆነ ቁጥሩ ከዚህም ሊልቅ ይችላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አይኤስ በአፍጋኒስታን የታሊባን አገዛዝን የሚቃወም ሁነኛ ተገዳዳሪ ሆኖ እየወጣ ነው።ይህ ቡድን በተለይ በሺአ ሙስሊሞች ላይ ተከታታይ ጥቃት በማድረስ ይታወቃል።ታሊባኖች የአሜሪካን ጦር ከካቡል መልቀቅን ተከትሎ አገሪቱን በእጃቸው ካስገቡ በቅርብ አንድ ዓመት እንደሆናቸው የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል፡፡

## ጃፓን ምጣኔ ኃብቷን ለማሳደግ ወጣቶች መጠጥ እንዲጠጡ ዘመቻ ጀመረች

ወጣቱ ዜጋ መጠጥ አልጠጣ ያላት ጃፓን መጠጥን ለማበረታት ባለሥልጣናቱ አዲስ ዘመቻን ከፍተዋል።ወጣቱ ትውልድ ከወላጆቻቸው ባነሰ ሁኔታ አልኮል እንደሚጠጡ መረጃዎች የጠቆሙ ሲሆን ይህም በአገሪቱ ሴክ ተብሎ ከሚጠራውን የሩዝ ወይን የሚገኘውን ግብር በከፍተኛ ሁኔታ ጎድቶታል ተብሏል።ይህንንም ለመቀልበስ የአገሪቱ የግብር ኤጀንሲ ብሔራዊ ዘመቻን ጀምሯል።

ዘመቻው “ሴክ ቪቫ” ይሰኛል፤ መጠጥን የበለጠ ለወጣቱ አጓጊ ለማድረግ እና በዚህ ኢንዱስትሪውን ለማሳደግም አቅዷል።በዚህም ዘመቻ ከ20 እስከ 39 ዓመት የሆናቸውን ወጣቶች የሚያሳትፍ ውድድር ተዘጋጅቷል።ወጣቶቹ የጃፓን መጠጥ የሆኑትን ሴክ፣ ሾቹ፣ ዊስኪ፣ ቢራና ወይን ላይ ያላቸው የቢዝነስ ሐሳቦች እንዲያካፍሉም ተጠይቀዋል።የግብር ባለሥልጣናቱን በመወከል ውድድሩን እያዘጋጀ ያለው ድርጅት እንዳለው በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት የመጠጥ ሽያጭ መቀነሱን አስታውቋል።



ለዚህም የተጠቀሱት ምክንያቶች በወረርሽኙ ምክንያት አዲስ የኑሮ ዘይቤ በመምጣቱ በተለይም የአገሪቱን መጠጥ በመግዛት የአንበሳ ድርሻ የነበረው በዕድሜ ተለቅ ያለው ዜጋም መጠጥ በመቀነሱ ነው ተብሏል።ተወዳዳሪዎች የማስተዋወቂያ ሐሳቦችን፣ የምርት ስያሜዎች እንዲሁም ላቅ ያሉ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን በመጠቀም የቴክኖሎጂ ውጤቶችን አዘጋጁ ተብለዋል።

የጃፓን መገናኛ ብዙኃን ምላሹ የተደበላለቀ ነው ብሏል። በተለይም ጤናማ ያልሆነ ልማድን ለማሳደግ በተከፈተው ዘመቻ ላይ ትችቶችና ወቀሳዎች እየተስተናገዱ ነው።ነገር ግን ሌሎች ያልተለመዱ ሐሳቦችንም በኢንተርኔት እያጋሩ ይገኛሉ። ለምሳሌም ያህል ታዋቂ ተዋናዮች በዲጂታል ክለቦች እንደ አስተናጋጅነት የሚሰሩበት ምናባዊ እውነታዎችንም ፈጥረው በማስተዋወቅ ላይ ናቸው።

ተወዳዳሪዎች ሐሳቦቻቸውን ለማቅረብ እስከ መስከረም መጨረሻ ድረስ ቀነ ገደብ ተሰጥቷቸዋል። የዘመቻው ድረ-ገጽ የጃፓን የአልኮል ገበያ እየቀነሰ መምጣቱን እና ለዚህም የአገሪቱ የዕድሜ ባለጸጎች ሞት እና የወሊድ መጠን ማሽቆልቆል ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው ብሏል።

ከግብር ኤጀንሲ የተገኙ የቅርብ ጊዜ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአውሮፓውያኑ 1995 ይጠጣ ከነበረው 100 ሊትር በሳምንት በ2020 ወደ 75 ሊትር መቀነሱን ቢቢሲ ዘግቧል።

Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ዓርብ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ዋልያዎቹ በወዳጅነት ጨዋታ ዛሬ ዩጋንዳን ይገጥማሉ

ቦጋለ አበበ

በአገራቸው ሊጎች ብቻ የሚጫወቱ ተጫዋቾች የሚሳተፉበት የአፍሪካ ዋንጫ(ቻን) ለመሳተፍ የመቶ ሰማንያ ደቂቃ ፍልሚያ ብቻ የሚቀረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋልያዎቹ) ዛሬ በወዳጅነት ጨዋታ የዩጋንዳ ብሔራዊ ቡድንን ይገጥማሉ። ሁለቱ ብሔራዊ ቡድኖች የሚያደርጉት ሁለት የአቋም መለኪያ ጨዋታ የሚካሄድበት ቀን በተደጋጋሚ ሲቀያየር የቆየ ቢሆንም ዛሬና የፊታችን እሁድ እንደሚካሄድ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ሁለቱም ግጥሚያዎች አዳማ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ስታዲየም ላይ የሚደረጉም ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንን ለወዳጅነት ጨዋታ በተደጋጋሚ የሚገጥሙት የዩጋንዳ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝ ሰርዲዮቪች ሚሉቲን ሚቾ አሁንም ከዋልያዎቹ ጋር ሁለት የወዳጅነት ጨዋታ ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል። በቀድሞ የቅዱስ ጊዮርጊስ አሰልጣኝ ሰርዮቪች ሚሉቲን ሚቾ የሚመራው የዩጋንዳ ብሔራዊ ቡድን እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ በቻን ውድድር የመጨረሻ የማጣሪያ ጨዋታ ከታንዛንያ አቻው ጋር ጠንካራ ፍልሚያ ይጠብቀዋል።

በአልጄሪያ አስተናጋጅነት ለሚከናወነው የቻን ውድድር ለማለፍ የመጨረሻ የማጣሪያ ጨዋታቸውን ከሩዋንዳ ብሔራዊ ቡድን ጋር ነሐሴ 20 እና ነሐሴ 29 የሚያከናውኑት ዋልያዎቹ ዝግጅታቸውን ከቀናት በፊት በአዳማ ማድረግ እንደጀመሩ ይታወቃል።

ደቡብ ሱዳንን በድምር ውጤት 5-0 አሸንፎ የመጨረሻውን ዙር ማጣሪያ የተቀላቀለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከሳምንት በፊት መሰባሰቡ የሚታወስ ሲሆን፣ በአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ጥሪ ከቀረበላቸው ተጫዋቾች መካከል ሱራፌል ዳኛቸው በጉዳት ምክንያት በወንድማገኝ ኃይሉ ከመተካቱ በስተቀር የቡድኑ አባላት በሙሉ ጤንነት ላይ ይገኛሉ።



ዋልያዎቹ ለመጨረሻው የቻን ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ ይረዳቸው ዘንድ ዛሬና እሁድ ከዩጋንዳ ጋር የወዳጅነት ጨዋታ ያደርጋሉ፣

የፊታችን ነሐሴ 20 እና 29 የደርሶ መልስ ጨዋታውን የሚያደርገው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ልምምዱን በአዳማ በመቀጠል ነሐሴ 18 የሜዳ ጨዋታውን ወደሚያደርግበት ታንዛንያ እንደሚያመራ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከሩዋንዳ ብሔራዊ ቡድን ጋር የሚያደርገው የማጣሪያ ጨዋታ የሚከናወንበት ቀናት እና ቦታዎች በሳምንቱ መጨረሻ ይፋ መደረጉ ይታወቃል። በዚህም በመጀመሪያው ጨዋታ ዋልያዎቹ ባለሜዳ ሆነው ነሐሴ 20/2014 ታንዛንያ ቤንጃሚን ምካፓ ስታዲየም ላይ ጨዋታቸውን የሚያደርጉ ይሆናል። የመልሱን ጨዋታ ደግሞ ነሐሴ 29/2014 ሩዋንዳ ላይ እንደሚደረግ የወጣው መርሐ ግብር ያሳያል።

በቅድመ ማጣሪያ ጨዋታው ከደቡብ ሱዳን ጋር የተደለደለችው የኢትዮጵያ ስቴድየሞች የካፍን መመዘኛ መስፈርት አለማሟላታቸውን ተከትሎ በተጣለው ዕገዳ ልክ እንደ አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎቿ ሁሉ ይህንንም ጨዋታ ከሜዳዋ ውጪ ታንዛኒያ ላይ ለማድረግ ተገዳለች።

የመጨረሻውን የማጣሪያ ጨዋታም ኢትዮጵያ እና ተጋጣሚዋ ሩዋንዳ የካፍን መስፈርት የሚያሟላ ስታዲየም የሌላቸው መሆኑን ተከትሎ እገዳ ላይ ቢገኙም ሩዋንዳ ቀናት በፊት አንድ ስቴድየሟ ጨዋታ እንዲያስተናግድ ፍቃድ ማግኘቱ ታውቋል። ይህንን ተከትሎ ሩዋንዳ ነሐሴ 29 የሚደረገውን የመልስ ጨዋታ በሁዬ ዓለም አቀፍ ስታዲየም እንደምታስተናግድ ይፋ ተደርጓል። ኢትዮጵያ ግን አሁንም ስቴድየሞቿ ፍቃድ ስላላገኙ ከሩዋንዳ ጋር ነሐሴ 20 የሚደረገውን የመጀመሪያ ጨዋታ በታንዛኒያ ዳሬሰላም ቤንጃሚን ምካፓ ስታዲየም እንደምታደርግ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ገልጿል።

በአፍሪካ ከዋናው አፍሪካ ዋንጫ ቀጥሎ ትልቁ የእግር ኳስ መድረክ የሆነው የቻን ዋንጫ በአገር ውስጥ ሊጎች የሚጫወቱ ተጫዋቾችን ብቻ ለማበረታታት በካፍ አማካኝነት እኤአ በ2007 የተዋወቀ ሲሆን 2009 ላይ በኮትዲቯር አዘጋጅነት ለመጀመሪያ ጊዜ ተካሂዷል። ከጊዜ ወደ ጊዜ በውድድሩ የሚሳተፉ አገራት ቁጥርም እያደገ ሄዶ ትኩረት ከሚሰጣቸው የስፖርት መድረኮች አንዱ ሆኗል። የዓለምን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራው ፊፋም እኤአ 2010 ላይ ለዚህ ውድድር እውቅና ሰጥቶታል።

ኢትዮጵያ ከሰላሳ አንድ ዓመታት በኋላ እኤአ 2013 ላይ በደቡብ አፍሪካ አዘጋጅነት በተካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ መሳተፏን ተከትሎ በእግር ኳሱ የተፈጠረው ከፍተኛ መነቃቃት ይታወሳል። የዚያ ትውልድ ታሪካዊ ተጫዋቾችና የዋልያዎቹ አሰልጣኝ የነበሩት ሰውነት ቢሻው ከአፍሪካ ዋንጫው ማግስት በተመሳሳይ ደቡብ አፍሪካ ላይ በተካሄደው የቻን ዋንጫ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ መሳተፍ ችለዋል። ለዚህ ተሳትፎም የመጨረሻውን የማጣሪያ ጨዋታ ከሩዋንዳ ጋር ከሜዳቸው ውጪ ተፋልመው ማለፋቸው አይዘነጋም።

ዋልያዎቹ በቀጣዩ የቻን ውድድርም በአሰልጣኝ ዮሐንስ ሳህሌ እየተመሩ በጋቦን በተካሄደው ዋንጫ ላይ መሳተፍ ችለዋል። በሁለቱም ብቸኛ ተሳትፏቸው ግን ከምድባቸው ሳያልፉ ቀርተዋል።

ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## ለሌሎች ተቋማት አርአያ የሚሆነው ተቋም «በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት»

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የፐብሊክ ሰራተኛው በከተማው ባለው የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ምክንያትት ይደርስበት የነበረ ወከባ፣ እንግልትና ወጪ በማስቀረት ምቾቱና ደህንነቱ ተጠብቆ በሚፈለገው ጊዜና ፍጥነት በአስተማማኝ ሁኔታ ወደ ስራና ቤቱ በማድረስ ረገድ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ በየጊዜው አደረጃጀቱንና የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል ላይ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅትም ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች አገልግሎት ከመስጠት ባሻገርም ከስራ መግቢያና መውጫያ ሰዓት ውጪ የዘመኑ ቴክኖሎጂ በተገጠመላቸው ምቾታቸው አስተማማኝ በሆኑ አውቶቡሶች የሕዝብ ትራንስፖርት ታክሲ አገልግሎት እየሠጠም ይገኛል።

የአገልግሎት አድማሱን ከፍ በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ተለያዩ ክፍለ አገሮች የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ መስጠት ተሸጋግሯል። በአሁን ወቅትም በሌላ ምእራፍ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ በመክፈት አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።





የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች ከቀናት በፊት የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎትን የስራ እንቅስቃሴ ጎብኝተዋል። አቶ ደንጌ ቦሩ በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር የሎጀስቲክስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ እንዲሁም ክቡር አቶ በርዖ ሀሰን የትራንስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ በተለይ በቅርቡ ተመርተው አገልግሎት መስጠት የሚጀምሩትን ልዩ ሀገር አቋራጭ አውቶቡሶች ጎብኝተዋል።

በዚሁ ወቅት የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬሕይወት ትልቁ ‹‹ልዩ ሀገር አቋራጭ አውቶቡሶቹ በተለይ አደጋን ተከላክሎ ለማሽከርከር የሚያስችሉ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው ፣ አሽከርካሪውን ለአደጋ የሚያጋልጡ ተግባራት ሲፈፀሙ ቀጥታ ለተቆጣጣሪው አካል ሪፖርት የሚያደርጉ መሆናቸው ለየት እንደሚያደርጋቸው ገልጸዋል።

ዘመናዊዎቹ አውቶቡሶች ተሳፋሪው ምቾትን የሚያላብሱ መጸዳጃ ቤት፣ ዋይፋይ በየመቀመጫው ሞባይል ቻርጀር ያላቸው፣ ሰፊ ዕቃ መጫኛና ለአካል ጉዳተኞች ሊፍት የተገጠመላቸው” መሆናቸውንም አብራርተዋል።

የድርጅቱ የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ በሚኒስትሮቹ ከተጎበኙት መካከል ይገኝበታል። ማሰልጠኛ ማዕከሉም አደጋን ተከላክሎ በማሽከርከር ክህሎት የተካኑ በትክክለኛው መንገድ ‹‹ማሽከርከርን ክቡር ሙያ ነው›› ብለው የሚያምኑ አሽከርካሪዎችን ለማፍራት ሰልጣኞችን በመቀበል ላይ እንደሆነ የገለጹት ዋና ዳይሬክተሯ፣ ሌሎችም የተቋሙን እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በጉብኝቱ ላይ የተገኙት አቶ ደንጌ ቦሩ በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር የሎጀስቲክስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ እንዲሁም ክቡር አቶ በርዖ ሀሰን የትራንስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በሁለንተናዊ የለውጥ ሒደት ውስጥ እንደሚገኝ ገልጸዋል።



በተመለከቱት አዳዲስ አሰራሮችና የስራ እንቅስቃሴ መደሰታቸውን ገልጸው፣‹‹ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ለሌሎች ተቋማት አርአያ የሚሆን በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው›› ብለዋል።

የሰራተኞች የስፖርት ጂምናዚየም ፣የሰራተኞች ልጆች ዴይኬር፣ የጓሮ አትክልት ልማትና የተሽከርካሪ ጥገና ማእከል በሚኒስትሮቹ ጉብኝት ከተካተቱት መካከል ተጠቃሾች ናቸው።